# ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!!

# ሕገ-ኢትዮድያ

## ፕ ሪ አ ም ብ ል (preamble)

**እኛ የኢትዮጵያ ህዝብ በአገራችን በኢትዮድያ ውስጥ**

**እስከ አንድ ሰው መብት ድረስ እንዲጠበቅ እና**

**ለሁሉም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በዕኩልነት መብታችንን ለማረጋገጥ፥**

**ከመንግስት በላይ የነጻነታችን ዋስትና ሆኖ እንዲቀመጥ፥**

**ይህ የህግ በላይነት ሰነድ ሕገ-ኢትዮድያን፥**

**በኢትዮጵያ ሕዝብ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጽፈን**

**ለእኛና ለሚመጣው ትውልድ የፍትሕ ሰነድ ሆኖ፥**

**ለዘለዓለም እንዲያገለግለን ይህ የሕገ-ኢትዮጵያ ሰነድ**

**በመስከረም 1 ቀን 2009 ዓ.ም ተፃፈ።**

የኢትዮጵያ የሕግ በላይነት ሥርዓት <u>ሕገ-ኢትዮጵያ</u> ተብሎ ይጠራል።

ሕገ-ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ መንግሥት መመዘኛ መሠረት ለሕዝባችን 9 ዋና ዋና ጥቅሞችን ያስገኛል።

1) መንግሥት ከሕዝብ በታች ፤ ሕዝብ ከመንግሥት በላይ እንዲሆን ያደርጋል።

2) የመንግሥት ምዝበራንና ጉቦን ያጠፋል ፤ የአገራችንን ኢኮኖሚ በፍጥነት ያሳድጋል።

3) መንግሥት የሚሠራውን ሁሉ ለሕዝብ በግልጽ እያሳወቀ እንዲሠራ ያዛል።

4) መሠረታዊ የሕዝብ ነፃነት እስከ አንድ ሰው መብት ድረስ ያስጠብቃል።

5) ማንኛውም ወንጀል፣ የፖለቲካ ወንጀልን ጨምሮ በአገራችን ውስጥ የሕዝቡን ሠላምና ፀጥታ የሚያውክ ነገር እንዳይኖር ያደርጋል ፤ ሕዝብ ያቀራርባል።

6) ያለ አግባብ የመንግሥት ተፅዕኖ በሕዝቡ ላይ እንዳይደርስ ይከለክላል።

7) ሁሉም ሰው ትክክለኛ ፍርድ በዕኩልነት እንዲያገኝ ያደርጋል።

8) የወንጀል ምርመራ አግባብ ባለው ምርምር እንጂ ቶርች፣ ግርፋት፣ እና ምንም ዓይነት በሰውነት ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ይከለክላል።

9) ማንኛውም ሰው ፍርዱን በስውር ሣይሆን በግልጽ በበቂ መረጃና በምስክሮች ማረጋገጫ ብቻ ፍርዱን እንዲቀበል ያደርጋል።

# ምዕራፍ አንድ

# ጠቅላላ ድንጋጌዎች

## ሕገ-ኢትዮጵያ የፌደራል መንግስት መዋቅር፥

በሕገ-ኢትዮጵያ የፌደራል መንግስት አስተዳደርን ሚዛን ለመጠበቅና ለመቆጣጠር እንዲቻል ዕኩል ስልጣን ያላቸው ሦስት ዋና የመንግስት ቅርንጫፎች አሉት።

ሶስቱ የኢትዮድያ ፌደራል መንግስት አካላት

## 1) ማዕከላዊ

ፕሬዚዴንትና  ካቢኔዎች

## 2) የሕዝብ ምክር ቤት

1) ሕግ አውጭና የሕግ መወሰኛ ተብሎ ይጠራል።
2) የሴናተሮች ወለልና የሕዝብ ተወካዮች ወለል ያጠቃልላል።
3) ሁለቱ ወለሎች፣ ሴናተሮችና የሕዝብ ተወካዮች ወለል አንድ ላይ የሚያደርጉት ጉባዔ የሕዝብ ምክር ቤት ጉባዔ ተብሎ ይጠራል።
4) 3 ሴናተሮች ከየ-ክፍለ ሀገር ይመረጣሉ።
5) አንድ የሕዝብ ተወካይ ከየ-አውራጃው ይመረጣል።

## 3) ሕግ አስፈፃሚና ሕግ ተርጓሚ ናቸው።

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የሕግ የበላይነት ፍርድ ቤት ናቸው።

# አንቀጽ 1

***የኢትዮጵያ መንግሥት ስያሜ***

*ሕገ ኢትዮጵያ ፌዴራላዊና ዴሞክራሲያዊ የመንግሥት አወቃቀር ይደነግጋል፡፡*

*በዚህ መሰረት የኢትዮጵያ መንግሥት **የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ** በሚል ሥያሜ ይጠራል፡፡*

# አንቀጽ 2

# *የኢትዮጵያ የግዛት ወሰን*

1) የኢትዮጵያ የግዛት ወሰን የፌዴራሉን አባሎች ወሰን የሚያጠቃልል ሆኖ በዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሰረት የተወሰነው ነው፡፡
2) የኢትዮዽያ ሰሜናዊ ድንበሯ በታህሣሥ 2 ቀን 1950 ዓ/ም በኒውዮርክ ላይ አምስተኛ የተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ከኤርትራ በተለየ ሙሉ ስልጣን ለኢትዮዽያ በመስጠት በደነገገው ውሳኔ መሠረት ኢትዮዽያ በባሕር ወደቦች በምፅዋና በአሰብ ላይ የባሌበትነት ሙሉ ስልጣን ይኖራታል ተብሎ በUnited Nation አንቀጽ ወይም ሪዞሉሽን Resolution Nu. 390V በንዑስ ቁጥር 2 ላይ ተደንግጓል።
3) በUnited Nation Resolution Nu. 390V ላይ ኤርትራ ከኢትዮዽያ እለያለሁ ካለች የአሰብን ወደብ የግድ ለኢትዮዽያ አሣልፋ መስጠት አለባት የሚል ነው፣ ወይም Eritrea must cede the port of Asseb to Ethiopia ይላል፣ ስለዚህ የኢትዮዽያ ሰሜናዊ ድንበር የአሰብ ወደብና የዳህላክ ደሰቶችን ጨምሮ ይከልላል።
4) በዓለም አቀፍ ሕግ መሠረት የተባበሩት መንግስታት ያፀደቀውን የተባበሩት መንግስታት ብቻ ማፍረስ አለበት። ስለዚህ የኢትዮዽያ ሰሜናዊ ድንበር በUnited Nation Resolution Nu. 390V ላይ ብቻ የፀና ይሆናል።
5) የኢትዮዽያ ሰሜናዊ ድንበር በ League of nations ላይ ኢትዮጵያ በሕጋዊ ካርታ ባስመዘገበችው መሠረት ብቻ የፀና ይሆናል።

# አንቀጽ 3

# የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ

የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ከላይ አረንጓዴ፣ ከመሐል ቢጫ፣ ከታች ቀይ ሆኖ በመሐሉ ምንም አርማ የለውም። ሦስቱም ቀለማት እኩል ሆነው አግድም ይቀመጣሉ፡፡



# አንቀጽ 4

# የኢትዮጵያ ፕሬዚዳንት ለመሆን የሚያበቁ መስፈርቶች

1) ለኢትዮጵያ ፕሬዚዴንት የምርጫ አፈጻጸም ሕግ፣ **“አንድ ድምፅ ለአንድ ሰው”** በሚለው መርሆ መሠረት ብቻ ይከናወናል።
2) ለኢትዮድያ ፕሬዚዴንት በአንቀጽ 39 ላይ ከተጠቀሱት ከ 3 መንግስት ፓርቲዎች መካከል ተወዳድሮ በችሎታው ያሸነፈ ወይም ያሸነፈች ግለሰብ ብቻ ይሆናል ወይም ትሆናለች።
3) የኢትዮድያ ፕሬዚዴንት ለመሆን የጾታ ገደብ የለውም።
4) የኢትዮድያ ፕሬዚዴንት ሴትም ሆነ ወንድ የዕድሜ መነሻ ከ35 አመት በላይ ሆኖ በአባቱም በእናቱም ኢትዮጵያዊ ሆኖ በኢትዮድያ ውስጥ ወይም በውጭ አገር ላይ የተወለደ ወይም የተወለደች መሆን አለባት።
5) ማንኛውም ለፕሬዚዴንትነት ውድድር መቅረብ የሚፈልግ ሰው ከሕዝባዊ ፓርቲ (ሕፓ) ወይም ከዴሞክራቲክ ፓርቲ (ዴፓ) ወይም ከ**ፌዴራል ፓርቲ (ፌፓ)** መካከል ተወዳድሮ በችሎታው ያሸነፈ ወይም ያሸነፈች ግለሰብ ብቻ ይሆናል ወይም ትሆናለች። ከዚህ ውጭ የሚመጣ ግለሰብ ወይም ፓርቲ ለኢትዮጵያ ፕረዚዴንትነት ለመወዳደር እንደማይችሉ መስፈርቱ በጥብቅ ይከለክላል።

# የኢትዮጵያ ፕሬዝዳንት የሥራ ድርሻ

# በሕገ ኢትዮጵያ ፕሬዚዴንቱን ጨምሮ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ከሕገ-ኢትዮጵያ በታች ነው ወይም ናት።

1) የኢትዮድያ ፕሬዚዴንት የአገሪቱ የበላይ መሪ ነው።
2) የኢትዮጵያ ፕሬዚዴንት ከሕገ-ኢትዮጵያ በታች ነው።
3) በአገሪቱ ውስጥ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊነት ያለበት ተመራጭ የአገር መሪ ነው።
4) ለሕገ ኢትዮድያ በመታዘዝ በታማኝነት አገሪቱን ይመራል።
5) የኢትዮድያ ፕሬዚዴንት ለ4 ዓመት አገልግሎት ብቻ ይመረጣል። ይሁንና ለሁለተኛ ጊዜ መወዳዳርም ይችላል።

6) የኢትዮድያ ፕሬዚዴንት ከሁለት ጊዜ በላይ እንዲወዳደር ሕገ-ኢትዮጵያ አይፈቅድም።
7) የኢትዮጵያ ፕሬዚዴንት የሕዝብ ተወካዮችን ምክር ቤት ውሳኔ የመቃወም መብት የለውም። ማንኛውም የፕሬዚዴንትን ተቃውሞ የሕዝብ ምክር ቤት በ2/3 (በሁለት ሶስተኛ) ድምጽ ውድቅ ማድረግ ይችላል።
8) ፕሬዚዴንት ምንም ዓይነት ጦርነት ማወጅ አይችልም። ነገር ግን ጦርነት ማወጅ የሚችለው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መንግስት ብቻ ነው።

## ምክትል ፕሬዚዴንት

1) ምክትል ፕሬዚዴንት ዕጩ የሚመርጠው ፕሬዚዴንቱ ነው። ነገር ግን የሚያጽድቀው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነው።

2) ፕሬዚዴንቱ በድንገት ከሞተ ወይም ከሞተች ወዲያውኑ ምክትል ፕሬዚዴንት የኢትዮጵያ ፕሬዚዴንት ይሆናል ወይም ትሆናለች።
3) ፕሬዚዴንቱ በስልጣን ከባለገ መጀመሪያ ወደ ፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይቀርባል ወይም ትቀርባለች። ቀጥሎ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መንግሥት በሁለት ሶሥተኛ ድምጽ ይባረራል/ትባረራለች።

4) ፕሬዚዴንቱና ም/ፕሬዚዴንቱ በድንገት ቢሞቱ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የበላይ ጠባቂ በጊዚያዊነት ሃገሪቷን ይመራል።

# የክፍለ ሀገር ዋና አስተዳደር

**ከሕገ-ኢትዮጵያ በታች ነው**

፩) የክፍለ ሀገሩ ዋና አስተዳደር ከፍተኛ የሥራ ኃላፍነት ያለበት ተመራጭ ነው ወይም ነች።

፪) የክፍለ ሀገሩ ዋና አስተዳደር የጾታ ልዩነት አይገድበውም።

፫) የክፍለ ሀገሩ ዋና አስተዳደር የዕድሜ መነሻ 35 ዓመት እና ከዛ በላይ መሆን አለበት።

፬) የክፍለ ሀገሩ ዋና አስተዳደር መሆን የሚችለው የክፍለ ሀገሩ ተወላጅ ወይም የክፍለ ሀገሩ ነዋሪ ቋንቋውንና ባሕሉን የሚያውቅ መሆን አለበት።

**የክፍለ ሀገሩ ዋና አስተዳደር የሥራ ድርሻ/ አብዘኛውን የክፍለ ሀገሩ ሕግ ይወስናል።**

፭) ከሕገ-ኢትዮጵያ በታች ክፍለ ሀገሩ ለሚያወጣው ሕግ በመታዝዝ በታማኝነት ክፍለ ሀገሩን ለ4 አመት ይመራል።

፮) የክፍለ ሀገሩ ዋና አስተዳደር ለ4 አመት አገልግሎት ብቻ ይመረጣል። ነገር ግን ለሁለተኛ ጊዜ መወዳደር ይችላል።

፯) የክፍለ ሀገሩ ዋና አስተዳደር ለ3ኛ ጊዜ እንዲወዳደር ሕገ ኢትዮጵያ አይፈቅድም።

፰) የክፍለ ሀገሩ ዋና አስተዳደር የክፍለ ሀገሩ ምክር ቤት ያሳለፈውን ውሳኔ የመቃወም መብት አለው። ነገር ግን የክፍለ ሀገሩ ምክር ቤት በ2/3 (በሁለት ሶስተኛ) ድምፅ ተቃውሞውን ውድቅ ሊያደርገው ይችላል።

፱) የክፍለ ሀገሩ ዋና አስተዳደር በድንገት ከሞተ ወይም ከሞተች ወዲያውኑ ምክትል አስተዳደር የክፍለ ሀገሩ ዋና አስተዳደር ይሆናል ወይም ትሆናለች።

፲)     የክፍለ ሀገሩ ዋና አስተዳደር በስልጣን ከባለገ መጀመሪያ ወደ ክፍለ ሀገሩ ፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይቀርባል ወይም ትቀርባለች። ቀጥሎ የክፍለ ሀገሩ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 2/3 (በሁለት ሶስተኛ) ድምጽ ያባርሩታል/ያባርሯታል።

# የክፍለ ሀገሩ ምክትል አስተዳደር

ዕጩውን የሚመርጠው የክፍለ ሀገሩ ዋና አስተዳደር ነው። ነገር ግን የሚያጸድቀው የክፍለ ሀገሩ የሕዝብ ምክር ቤት ይሆናል።

# አንቀጽ 5

# ፌዴራል ዴሞክራቲክ ሪፑብሊክ ኢትዮጵያ

# የሕግ አስፈፃሚና የሕግ ተርጓሚ መንግሥት

1. በቀጥታ በሕዝብ የተመረጡ 7 ዳኞች ይኖሩታል። እነዚህ ሰባቱ ዳኞች ከማንኛውም ፓርቲ ነፃ የሆኑ መሆን አለባቸው።
2. በተለይም በአንቀፅ 39 የተደነገጉ ፓርቲዎች:
   ሀ) **ሕዝባዊ ፓርቲ (ሕፓ)**
   ለ) **ዴሞክራትክ ፓርቲ (ዴፓ)**
   ሐ) ***ፌዴራል ፓርቲ (ፌፓ)*** ነፃ የሆኑ መሆን አለባቸው።
3. የኢትዮጵያ ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዋና ጽሕፈት ቤት በኢትዮጵያ ዋና ከተማ በአዲስ አበባ ውስጥ ይሆናል።
4. የኢትዮጵያ ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከ13ቱ ክፍላተ ሀገሮች በሚመጡት የይግባኝ ውሳኔዎች ላይ የመጨረሻ ፍርድ ይወስናል።

4. የኢትዮድያ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኞች የአገልግሎት ዘመናቸው 6 አመት ብቻ ይሆናል፣ ነገር ግን በየ 6 ዓመት በአገራዊ ምርጫ ላይ እንደገና መወዳደር ይችላሉ።

5. የኢትዮጵያ ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኞች በየ6 አመት እንደገና ለመመረጥ የጊዜ ገደብ የለባቸውም ።

6. የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገር ፍርድ ቤት ዳኞች የአገልግሎት ዘመናቸው 4 አመት ብቻ

ይሆናል። ነገር ግን በየ4 ዓመት በየክፍለ ሀገር ምርጫ ላይ እንደገና መወዳደር ይችላሉ።

7. የክፍለ ሀገር ዳኞች በየ4 አመት እንደገና ለመመረጥ የጊዜ ገደብ የለባቸውም።

8. የክፍለ ሀገር የኢትዮጵያ ፌዴራል ሕጎች በሕገ-ኢትዮድያ ሥር ሆነው እንደ ክፍለ ሀገሩ ሕጎች ይለያያሉ።

9. የኢትዮድያ የክፍለ ሀገር ፌዴራል ዳኞችን የሥራ ድርሻ አብዘኛውን የክፍለ ሀገሩ ሕግ ይወስናል።

# አንቀጽ 6

## የኢትዮጵያ ብሔራዊ መዝሙር

የኢትዮጵያ ብሔራዊ መዝሙር የሕገ-ኢትዮጵያን ዓላማዎችና የኢትዮጵያ ሕዝብ በዴሞክራሲ ሥርዓት አብረው ለመኖር ያላቸውን እምነት፣ እንዲሁም የወደፊት የጋራ ዕድላቸውን የሚያንጸባርቅ ሆኖ በሕግ ይወሰናል፡፡

# አንቀጽ 7

## ስለ ቋንቋ

1) ማናቸውም የኢትዮጵያ ቋንቋዎች በእኩልነት የመንግሥት እውቅና ይኖራቸዋል፡፡
2) አማርኛ የፌዴራሉ መንግሥት የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ የሥራ ቋንቋ ይሆናል፡፡

# አንቀጽ 8

## ስለ ዜግነት

1) ማንኛውም ግለሰብ ከወላጆቹ/ከወላጆቿ አንደኛቸው ኢትዮጵያዊ/ኢትዮጵያዊት የሆነ/የሆነች የኢትዮጵያ ዜጋ የመሆን መብቱ ይጠበቅበታል፡፡
2) ማንኛውም ግለሰብ ኢትዮጵያዊ/ኢትዮጵያዊት የሆነ/የሆነች የሁለት አገር ዜጋ የመሆን ሙሉ መብት አለው/አላት።
3) የውጭ ሀገር ዜጐች የኢትዮጵያ ዜግነት ከጠየቁ ሊያገኙ ይችላሉ፡፡

ዜግነትን በሚመለከት ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡

4) ማንኛውም ሰው ነጭም ሆነ ጥቁር በኢትዮጵያ ሀገር ላይ የተወለደ ሁሉ ያለ አንዳች ጥያቄ ኢትዮድያዊ ነው/ነች ፤ ወይም የኢትዮጵያ ሙሉ ዜጋ ነው/ነች፡፡

## አንቀጽ 9
## የፆታ አገላለጽ

በዚህ ሕገ-ኢትዮጵያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

# የሕገ-ኢትዮጵያ መሰረታዊ መርሆዎችና የሕዝብ ሉዓላዊነት

## አንቀጽ 10

## የሕገ-ኢትዮጵያ በላይነት

1) ሕገ-ኢትዮድያ የሀገሪቱ የበላይ ሕግ ነው፡፡ ማንኛውም ሕግ፣ ልማዳዊ አሰራር፣ እንዲሁም የመንግሥት አካል ወይም ባለሥልጣን ውሳኔ ከዚህ ሕግ ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡
2) ማንኛውም ዜጋ፣ የመንግሥት አካላት፣ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ሌሎች ማኅበራት እንዲሁም ባለሥልጣኖቻቸው፣ ሕግን የማስከበርና ለሕግ ተገዢ የመሆን ኃላፊነት አለባቸው፡፡
3) በዚህ ሕግ ከተደነገገው ውጭ በማናቸውም አኳኋን የመንግሥት ሥልጣን መያዝ የተከለከለ ነው፡፡
4) ኢትዮጵያ ያጸደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የሀገሪቱ ሕግ አካል ናቸው፡፡

## አንቀጽ 11
## የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች

1) ሰብዓዊ መብቶችና ነጻነቶች ከሰው ልጅ ተፈጥሮ የሚመነጩ፣ የማይጣሱና የማይገፈፉ ናቸው፡፡
2) የማንኛውም ዜጋ የግልና የቡድን ሰብዓዊና የዲሞክራሲ መብቱ የተከበረ ነው።
3) በሕገ ኢትዮጵያ ጠጥቶ ማሽከርከር ፈጽሞ የተከለከለ ነው።

# አንቀጽ 12
# የመንግሥትና የሃይማኖት መለያየት

1) መንግሥትና ሃይማኖት የተለያዩ ናቸው፡፡
   መንግሥታዊ ሃይማኖት አይኖርም፡፡

2) መንግሥት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም፡፡ ሃይማኖትም በመንግሥት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም፡፡

# አንቀጽ 13
# የመንግሥት አሠራርና ተጠያቂነት

1) የመንግሥት አሠራር ለሕዝብ ግልጽ በሆነ መንገድ መከናወን አለበት፡፡
2) ማንኛውም ኃላፊና የሕዝብ ተመራጭ ኃላፊነቱን ሲያጓድል ተጠያቂ ይሆናል፡፡ ሕዝብ በመረጠው ተወካይ ላይ እምነት ባጣ ጊዜ ከቦታው ለማንሳት ይችላል፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡

# አንቀጽ 14
# በሕይወት የመኖር

የአካል ደህንነትና የነጻነት ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ መብት በመሆኑ የማይደፈርና የማይገሰስ በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነትና የነጻነት መብት አለው፡፡

# አንቀጽ 15

# የሕይወት መብት

ማንኛውም ሰው በሕይወት የመኖር መብት አለው፡፡ ማንኛውም ሰው በሕግ በተደነገገ ከባድ የወንጀል ቅጣት ካልሆነ በስተቀር ሕይወቱን አያጣም፡፡

# አንቀጽ 16

## የአካል ደህንነት መብት

ማንኛውም ሰው በአካሉ ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት የመጠበቅ መብት አለው፡፡

# አንቀጽ 17

## የነጻነት መብት

1. በሕግ ከተደነገገው ሥርዓት ውጭ ማንኛውም ሰው ወንድም ሆነ ሴት ነጻነቱን/ቷን አያጣም/አታጣም፡፡
2. ማንኛውም ሰው በሕግ ከተደነገገው ሥርዓት ውጭ ሊያዝ፣ ክስ ሳይቀርብበት ወይም ሳይፈረድበት ሊታሰር አይችልም፡፡

# አንቀጽ 18

## ኢሰብዓዊ አያያዝ ስለመከልከል

1. ማንኛውም ሰው ጭካኔ ከተሞላበት፣ ኢሰብዓዊ ከሆነ ወይም ክብሩን ከሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት የመጠበቅ መብት አለው፡፡
2. ማንኛውም ሰው በባርነት ወይም በግዴታ አገልጋይነት ሊያዝ አይችልም። ለማንኛውም ዓላማ በሰው የመነገድ ተግባር የተከለከለ ነው፡፡
3. ማንኛውም ሰው በኃይል ተገዶ ወይም ግዴታ ለማሟላት ማንኛውንም ሥራ እንዲሠራ ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 «በኃይል ተገዶ ወይም ግዴታን ለማሟላት» የሚለው ሐረግ የሚከተሉትን ሁኔታዎች አያካትትም፤

ሀ/ ማንኛውም እስረኛ በእስራት ላይ ባለበት ጊዜ በሕግ መሠረት እንዲሠራ የተወሰነውን ወይም በገደብ ከእስር በተለቀቀበት ጊዜ፣ የሚሠራውን ማንኛውም ሥራ፣

ለ/ ማንኛውም ወታደራዊ አገልግሎት ለመስጠት ሕሊናው የማይፈቅድለት ሰው በምትክ የሚሰጠውን አገልግሎት፣

ሐ/ የማኅበረሰቡን ሕይወት ወይም ደህንነት የሚያሰጋ የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ወይም አደጋ በሚያጋጥምበት ጊዜ የሚሰጥ ማንኛውም አገልግሎት፣

መ/ በሚመለከተው ሕዝብ ፈቃድ በአካባቢው የሚፈጸመውን ማንኛውንም ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ የልማት ሥራ፡፡

# አንቀጽ 19

# የተያዙ ሰዎች መብት

1. ወንጀል ፈጽመዋል በመባል የተያዙ ሰዎች የቀረበባቸውን ክስና ምክንያቶቹ በዝርዝር ወዲያውኑ በሚገባቸው ቋንቋ እንዲነገራቸው መብት አላቸው፡፡
2. የተያዙ ሰዎች ላለመናገር መብት አላቸው፤ የሚሰጡት ማንኛውም ቃል ፍርድ ቤት በማስረጃነት ሊቀርብባቸው እንደሚችል መረዳት በሚችሉት ቋንቋ እንደተያዙ ወዲያውኑ ማስገንዘቢያ እንዲሰጣቸው መብት አላቸው፡፡
3. የተያዙ ሰዎች በአርባ ስምንት ሰዓታት ውስጥ ፍርድ ቤት የመቅረብ መብት አላቸው፡፡ ይህም ጊዜ ሰዎቹ ከተያዙበት ቦታ ወደ ፍርድ ቤት ለመምጣት አግባብ ባለው ግምት የሚጠይቀውን ጊዜ አይጨምርም፡፡ ወዲያውኑ ፍርድ ቤት እንደቀረቡ በተጠረጠሩበት ወንጀል ለመታሰር የሚያበቃ ምክንያት ያለ መሆኑ ተለይቶ እንዲገለጽላቸው መብት አላቸው፡፡
4. የያዛቸው የፖሊስ መኮንን ወይም የሕግ አስከባሪ በጊዜው ገደብ ፍርድ ቤት በማቅረብ የተያዙበትን ምክንያት ካላስረዳ፣ ፍርድ ቤቱ የአካል ነጻነታቸውን እንዲያስከብርላቸው የመጠየቅ ሊጣስ የማይችል መብት አላቸው፡፡ ሆኖም ፍትሕ እንዳይጓደል ሁኔታው የሚጠይቅ ከሆነ ፍርድ ቤቱ የተያዘው ሰው በጥበቃ ሥር እንዲቆይ ለማዘዝ ወይም ምርመራ ለማካሄድ ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ ሲጠየቅ አስፈላጊ በሆነ መጠን ብቻ ሊፈቅድ ይችላል፡፡ የሚያስፈልገውን ተጨማሪ ጊዜ ፍርድ ቤቱ ሲወስን ኃላፊ የሆኑት የሕግ አስከባሪ ባለሥልጣኖች ምርመራውን አጣርተው የተያዘው ሰው በተቻለ ፍጥነት ፍርድ ቤት እንዲቀርብ ያለውን መብት የሚያስከብር መሆን አለበት፡፡
5. የተያዙ ሰዎች በራሳቸው ላይ በማስረጃነት ሊቀርብ የሚችል የእምነት ቃል እንዲሰጡ ወይም ማናቸውንም ማስረጃ እንዲያምኑ አይገደዱም፡፡ በማስገደድ የተገኘ ማስረጃ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

6. የተያዙ ሰዎች በዋስ የመፈታት መብት አላቸው፡፡ ሆኖም በሕግ በተደነገጉ ልዩ ሁኔታዎች ፍርድ ቤት ዋስትና ላለመቀበል ወይም በገደብ መፍታትን ጨምሮ በቂ የሆነ የዋስትና ማረጋገጫ እንዲቀርብ ለማዘዝ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 20

## የተከሰሱ ሰዎች መብት

1. የተከሰሱ ሰዎች ክስ ከቀረበባቸው በኃላ ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ ውስጥ በመደበኛ ፍርድ ቤት ለሕዝብ ግልጽ በሆነ ችሎት የመሰማት መብት አላቸው፡፡ ሆኖም የተከራካሪዎቹን የግል ሕይወት፣ የሕዝብን የሞራል ሁኔታና የሀገሪቱን ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል ብቻ ክርክሩ በዝግ ችሎት ሊሰማ ይችላል፡፡
2. ክሱ በቂ በሆነ ዝርዝር እንዲነገራቸው እና ክሱን በጽሁፍ የማግኘት መብት አላቸው፡፡
3. በፍርድ ሂደት ባሉበት ጊዜ በተከሰሱበት ወንጀል እንደ ጥፋተኛ ያለመቆጠር፣ በምስክርነት እንዲቀርቡም ያለመገደድ መብት አላቸው፡፡
4. የቀረበባቸውን ማናቸውንም ማስረጃ የመመልከት፣ የቀረቡባቸውን ምስክሮች የመጠየቅ፣ ለመከላከል የሚያስችላቸውን ማስረጃ የማቅረብ ወይም የማስቀረብ እንዲሁም ምስክሮቻቸው ቀርበው እንዲሰሙላቸው የመጠየቅ መብት አላቸው፡፡
5. በመረጡት የሕግ ጠበቃ የመወከል ወይም ጠበቃ ለማቆም አቅም በማጣታቸው ፍትሕ ሊጓደል የሚችልበት ሁኔታ ሲያጋጥም ከመንግሥት ጠበቃ የማግኘት መብት አላቸው፡፡
6. ክርክሩ በሚታይበት ፍርድ ቤት በተሰጠባቸው ትእዛዝ ወይም ፍርድ ላይ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት አላቸው፡፡
7. የፍርዱ ሂደት በማይገባቸው ቋንቋ በሚካሄድበት ሁኔታ በመንግሥት ወጪ ክርክሩ እንዲተረጐምላቸው የመጠየቅ መብት አላቸው፡፡

## አንቀጽ 21

## በጥበቃ ሥር ያሉና በፍርድ የታሰሩ ሰዎች መብት

1. በጥበቃ ሥር ያሉና በፍርድ የታሰሩ ሰዎች ሰብዓዊ ክብራቸውን በሚጠብቁ ሁኔታዎች የመያዝ መብት አላቸው፡፡

2. ከትዳር ጓደኞቻቸው፣ ከቅርብ ዘመዶቻቸው፣ ከጓደኞቻቸው፣ ከሃይማኖት መሪ ዎቻቸው፣ ከሐኪሞቻቸው እና ከሕግ አማካሪዎቻቸው ጋር ለመገናኘትና እንዲጐበኟቸውም ዕድል የማግኘት መብት አላቸው፡፡

# አንቀጽ 22

# የወንጀል ሕግ ወደኋላ ተመልሶ የማይሰራ ስለመሆኑ

1. ማንኛውም ሰው የወንጀል ክስ ሲቀርብበት የተከሰሰበት ድርጊት በተፈጸመበት ጊዜ ድርጊቱን መፈጸሙ ወይም አለመፈጸሙ ወንጀል መሆኑ በሕግ የተደነገገ ካልሆነ በስተቀር ሊቀጣ አይችልም፡፡ እንዲሁም ወንጀሉን በፈጸመበት ጊዜ ለወንጀሉ ተፈጻሚ ከነበረው የቅጣት ጣሪያ በላይ የከበደ ቅጣት በማንኛውም ሰው ላይ አይወሰንም፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ቢኖርም፣ ድርጊቱ ከተፈጸመ በኋላ የወጣ ሕግ ለተከሳሹ ወይም ለተቀጣው ሰው ጠቃሚ ሆኖ ከተገኘ ከድርጊቱ በኋላ የወጣው ሕግ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

# አንቀጽ 23

# በአንድ ወንጀል ድጋሚ ቅጣት ስለመከልከሉ

ማንኛውም ሰው በወንጀል ሕግና ሥነ ሥርዓት መሠረት ተከሶ የመጨረሻ በሆነ ውሳኔ ጥፋተኛነቱ በተረጋገጠበት ወይም በነጻ በተለቀቀበት ወንጀል እንደገና አይከሰስም ወይም አይቀጣም፡፡

# አንቀጽ 24

# ስለ ቅጣትና ስለመከልከሉ

1) ማንኛውም ሰው በወንጀል ሕግና ሥነ ሥርዓት መሠረት ጠጥቶ ማሽከርከር በፌዴራል ሕግ የሚያስቀጣ ወንጀል ነው።
2) በሕገ-ኢትዮጵያ ማንኛውም ወጣት ዕድሜው ከ21 ዓመት በታች የሆነ ሁሉ መጠጣትና ማጨስ በፌዴራል ሕግ ወንጀል የሚያስቀጣ ነው።
3) በሕገ-ኢትዮጵያ ልጆች በፈጸሙት ወንጀል ወላጆች፣ ወላጆችም በፈጸሙት ወንጀል ልጆች፣ በአጠቃላይ የቤተሰብ አባላት የወንጀሉ ተባባሪዎች እስካልሆኑ ድረስ አይጠየቁም።

# አንቀጽ 25

## የክብርና የመልካም ስም መብት

ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ ክብሩና መልካም ስሙ የመከበር መብት አለው፡፡
ማንኛውም ሰው የራሱን ስብዕና ከሌሎች ዜጐች መብቶች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ በነጻ የማሳደግ መብት አለው፡፡ ማንኛውም ሰው በማንኛውም ስፍራ በሰብዓዊነቱ እውቅና የማግኘት መብት አለው፡፡

# አንቀጽ 26

## የእኩልነት መብት

ሁሉም ሰዎች በሕግ ፊት እኩል ናቸው፤ በመካከላቸውም ማንኛውም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግ በሕግ እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል፡፡ በዚህ ረገድ በዘር፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ፣ በማኅበራዊ አመጣጥ፣ በሀብት፣ በትውልድ ወይም በሌላ አቋም ምክንያት ልዩነት ሳይደረግ ሰዎች ሁሉ እኩልና ተጨባጭ የሕግ ዋስትና የማግኘት መብት አላቸው፡፡

# አንቀጽ 27

## የግል ሕይወት፣ የመከበርና የመጠበቅ መብት

1. ማንኛውም ሰው የግል ሕይወቱ፣ ግላዊነቱ፣ የመከበር መብት አለው፡፡ ይህ መብት መኖሪያ ቤቱ፣ ሰውነቱና ንብረቱ ከመመርመር እንዲሁም በግል ይዞታው ያለ ንብረት ከመያዝ የመጠበቅ መብትን ያካትታል፡፡ ነገር ግን ቤቱ የወንጀለኞች ሥራ የሚከናወንበት ሆኖ ከተጠረጠረ፣ ቤቱና ንብረቱ በወንጀል ተግባር በዘረፋና ሙስና በተገኘ ገንዘብ የተሰራ፣ ወይም የባንክ ዕዳ ያልተከፈለበት ከሆነ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሊፈተሽ ወይም ሊታገድ ይችላል ።
2. ማንኛውም ሰው በግል የሚጽፋቸውንና የሚጻጻፋቸው፣ በፖስታ የሚልካቸው ደብዳቤዎች፣ እንዲሁም በቴሌፎን፣ በቴሌኮሙኒኬሽንና በኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች የሚያደርጋቸው ግንኙነቶች አይደፈሩም፡፡
3. የመንግሥት ባለ-ሥልጣኖች እነዚህን መብቶች የማክበርና የማስከበር ግዴታ አለባቸው፡፡ አስገዳጅ ሁኔታዎች ሲፈጠሩና ብሔራዊ ደህንነትን፣ የሕዝብን ሰላም፣

ወንጀልን በመከላከል፣ ጤናንና የሕዝብን የሞራል ሁኔታ በመጠበቅ ወይም የሌሎችን መብትና ነጻነት በማስከበር ዓላማዎች ላይ በተመሰረቱ ዝርዝር ሕጐች መሰረት ካልሆነ በስተቀር የእነዚህ መብቶች አጠቃቀም ሊገደብ አይችልም፡፡

# አንቀጽ 28

## የሃይማኖት፣ የእምነትና የአመለካከት ነጻነት

1) ማንኛውም ሰው የማሰብ፣ የሕሊና እና የሃይማኖት ነጻነት አለው፡፡ ይህ መብት ማንኛውም ሰው የመረጠውን ሃይማኖት ወይም እምነት የመያዝ ወይም የመቀበል፣ ሃይማኖቱንና እምነቱን ለብቻ ወይም ከሌሎች ጋር በመሆን በይፋ ወይም በግል የማምለክ፣ የመከተል፣ የመተግበር፣ የማስተማር ወይም የመግለጽ መብትን ያካትታል፡፡ የሃይማኖት ተከታዮች ሃይማኖታቸውን ለማስፋፋትና ለማደራጀት የሚያስችሏቸው የሃይማኖት ትምህርትና የአስተዳደር ተቋማት ማቋቋም ይችላሉ፡፡
2) ማንኛውም ሰው የሚፈልገውን እምነት ለመያዝ ያለውን ነጻነት በኃይል ወይም በሌላ ሁኔታ በማስገደድ መገደብ ወይም መከልከል አይቻልም፡፡
3) ወላጆችና ሕጋዊ ሞግዚቶች በእምነታቸው መሰረት የሃይማኖታቸውንና የመልካም ሥነ ምግባር ትምህርት በመስጠት ልጆቻቸውን የማሳደግ መብት አላቸው፡፡
4) ሃይማኖትና እምነትን የመግለጽ መብት ሊገደብ የሚችለው የሕዝብን ደህንነት፣ ሰላምን፣ ጤናን፣ ትምህርትን፣ የሕዝብን የሞራል ሁኔታ፣ የሌሎች ዜችን መሰረታዊ መብቶች፣ ነጻነቶች እና መንግሥት ከሃይማኖት ነጻ መሆኑን ለማረጋረገጥ በሚወጡ ሕጐች ይሆናል፡፡

# አንቀጽ 29

## በሰብዕና ስለሚፈጸሙ ወንጀሎች

1. ኢትዮጵያ ባጸደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እና በሌሎች የኢትዮጵያ ሕጐች በሰው ልጅ ላይ የተፈጸሙ ወንጀሎች ተብለው የተወሰኑትን ወንጀሎች፤የሰው ዘር የማጥፋት፣ ያለፍርድ የሞት ቅጣት እርምጃ የመውሰድ፣ በአስገዳጅ ሰውን የመሰወር፣ ወይም ኢሰብዓዊ የድብደባ ድርጊቶችን በፈጸሙ ሰዎች ላይ ክስ ማቅረብ በይርጋ አይታገድም፡፡ በሕግ አውጪው ክፍልም ሆነ በማንኛውም የመንግሥት አካል ውሳኔዎች በምሕረት ወይም በይቅርታ አይታለፉም፡፡

# ዴሞክራሲያዊ መብቶች

# አንቀጽ 30

# የአመለካከት እና ሐሳብን በነጻ የመያዝና የመግለጽ መብት

1. ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት የመሰለውን አመለካከት ለመያዝ ይችላል፡፡
2. ማንኛውም ሰው ያለ-ማንም ጣልቃ ገብነት ሐሳቡን የመግለጽ ነጻነት አለው፡፡ ይህ ነጻነት በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ ወሰን ሳይደረግበት በቃልም ሆነ በጽሑፍ ወይም በሕትመት፣ በሥነ ጥበብ መልክ ወይም በመረጠው በማንኛውም የማሰራጫ ዘዴ፣ ማንኛውንም ዓይነት መረጃና ሐሳብ የመሰብሰብ፣ የመቀበልና የማሰራጨት ነጻነቶችን የካትታል፡፡
3. የፕሬስና የሌሎች መገናኛ ብዙኃን፣ እንዲሁም የሥነ ጥበብ ፈጠራ ነጻነት ተረጋግጧል፡፡ የፕሬስ ነጻነት በተለይ የሚከተሉትን መብቶች ያጠቃልላል፡፡

I.

ሀ/ የቅድሚያ ምርመራ በማንኛውም መልኩ የተከለከለ መሆኑን፣

II. ለ/ የሕዝብን ጥቅም የሚመለከት መረጃ የማግኘት ዕድልን፡፡

4. ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች፣ ሐሳቦችና አመለካከቶች በነጻ መንሸራሸራቸውን ለማረጋገጥ ሲባል ፕሬስ በተቋምነቱ የአሠራር ነጻነትና የተለያዩ አስተያየቶች የማስተናገድ ችሎታ እንዲኖረው የሕግ ጥበቃ ይደረግለታል፡፡
5. በመንግሥት ገንዘብ የሚካሄድ ወይም በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ያለ መገናኛ ብዙኃን የተለያዩ አስተያየቶችን ለማስተናገድ በሚያስችለው ሁኔታ እንዲመራ ይደረጋል፡፡
6. እነዚህ መብቶች ገደብ ሊጣልባቸው የሚችለው የሀሳብና መረጃ የማግኘት ነጻነት በአስተሳሰባዊ ይዘቱና ሊያስከትል በሚችለው አስተሳሰባዊ ውጤት ሊገታ አይገባውም በሚል መርህ ላይ ተመስርተው በሚወጡ ሕጎች ብቻ ይሆናል፡፡ የወጣቶችን ደህንነት፣ የሰውን ክብርና መልካም ስም ለመጠበቅ ሲባል ሕጋዊ ገደቦች በነዚህ መብቶች ላይ ሊደነገጉ ይችላሉ፡፡ የጦር ቅስቃሴዎች እንዲሁም ሰብዓዊ ክብርን የሚነኩ የአደባባይ መግለጫዎች በህግ የሚከለከሉ ይሆናል፡፡
7. ማንኛውም ዜጋ ከላይ በተጠቀሱት መብቶች አጠቃቀም ረገድ የሚጣሉ ሕጋዊ ገደቦችን ጥሶ ከተገኘ በሕግ ተጠያቂ ሊሆን ይየችላል፡፡

## አንቀጽ 31

## የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ

## ነጻነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት

1. ማንኛውም ሰው ከሌሎች ጋር በመሆን መሣሪያ ሳይዝ በሰላም የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነጻነትና፣ አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው፡፡ ከቤት ውጭ የሚደረጉ ስብሰባዎችና ሰላማዊ ሰልፎች በሚንቀሳቀሱባቸው ቦታዎች በሕዝብ እንቅስቃሴ ላይ ችግር እንዳይፈጥሩ ለማድረግ ወይም በመካሔድ ላይ ያለ ስብሰባ ወይም ሰላማዊ ሰልፍ ሰላምን፣ ዴሞክራሲያዊ መብቶችንና የሕዝብን የሞራል ሁኔታ እንዳይጥሱ ለማስጠበቅ አግባብ ያላቸው ሥርዓቶች ሊደነገጉ ይችላሉ፡፡
2. ይህ መብት የወጣቶችን ደህንነት፣ የሰውን ክብርና መልካም ስምን ለመጠበቅ፣ የጦርነት ቅስቀሳዎች እንዲሁም ሰብዓዊ ክብርን የሚነኩ የአደባባይ መግለጫዎችን ለመከላከል ሲባል በሚወጡ ሕጎች መሰረት ተጠያቂ ከመሆን አያድንም፡፡

## አንቀጽ 32

## የመደራጀት መብት

ማንኛውም ሰው ለማንኛውም ዓላማ በማኅበር የመደራጀት መብት አለው፡፡ ሆኖም አግባብ ያለውን ሕግ በመጣስ ወይም ሥርዓቱን በሕገ ወጥ መንገድ ለማፍረስ የተመሰረቱ ወይም የተጠቀሱትን ተግባራት የሚያራምዱ ድርጅቶች የተከለከሉ ይሆናሉ፡፡

## አንቀጽ 33

## የመዘዋወር ነጻነት

1. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወይም በሕጋዊ መንገድ ሀገሪቱ ውስጥ የሚገኝ የውጭ ዜጋ በመረጠው የሀገሪቱ አካባቢ የመዘዋወርና የመኖሪያ ቦታ የመመስረት፣ እንዲሁም በፈለገው ጊዜ ከሀገር የመውጣት ነጻነትትና መብት አለው፡፡
2. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወደ ሀገሩ የመመለስ መብት አለው፡፡

3. ከእንግዲህ ስደትን ለማስቀረት፤ **ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዕድሜው 18 ዓመት ሲሞላው ፓስፖርት** በተወለደበት አከባቢ ያለአንዳች ውጣውረድ የማግኘት ሙሉ መብት አለው።
4. ሴቶች እናቶችና አሣዳጊዎች ለልጆቻቸው **ከተወለደበት ዕለት ጀምሮ** ዕድሜያቸው **17** ዓመት እስኪሞላ ድረስ ፓስፖርት ለማስወጣት ሙሉ መብትና ኃላፊነት አለባቸው።
5. **ማንኛውም ኢትዮድያዊ ዕድሜው 18 ዓመት ሲሞላው ወደ ፈለገበት ውጭ አገር ሄዶ ፣ ሠርቶ፣ ወይም ተምሮ ለመመለስ ሙሉ መብት አለው።**

# አንቀጽ 34

**የዜግነት መብቶች**

1. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ/ኢትዮጵያዊት ከፈቃዱ/ከፈቃዷ ውጭ ኢትዮጵያዊ ዜግነቱን/ዜግነትዋን ሊገፈፍ ወይም ልትገፈፍ አይችልም/አትችልም፡፡ ኢትዮጵያዊ / ኢትዮጵያዊት ዜጋ ከሌላ ሀገር ዜጋ ጋር የሚፈጽመው/የምትፈጽመው ጋብቻ ኢትዮጵያዊ ዜግነቱን / ዜግነትዋን አያስቀርም፡፡
2. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ የኢትዮጵያ ዜግነት በሕግ የሚያስገኘውን መብት ጥበቃና ጥቅም የማግኘት መብት አለው፡፡ ይኼውም በውጭ አገር በመወለድ ወይም በመኖር የሌላ አገር ዜግነት ያገኙ ትውልደ ኢትዮጵያውያን የመኖሪያ ፈቃድ ሃብትና ንብረት የመያዝ መብታቸው በውጭ አገር የሚኖረውን ገንቢ ሃይል ለማሰባሰብና ፊቱን ወደ አገሩ እንዲመልስ የጣምራ ዜግነት (double nationality) መብት የተጠበቀ ነው።
3. ማንኛውም ዜጋ ኢትዮጵያዊ ዜግነቱን የመለወጥ መብት አለው፡፡
4. ኢትዮጵያ ከአጸደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ጋር በማይቃረን መንገድ በሚወጣ ሕግ እና በሚደነገግ ሥርዓት መሰረት የኢትዮጵያ ዜግነት ለውጭ ሀገር ሰዎች ሊሰጥ ይችላል፡፡

# አንቀጽ 35

## የጋብቻ፣ የግልና የቤተሰብ መብቶች

1. በሕግ ከተወሰነው የጋብቻ ዕድሜ የደረሱ ወንዶችና ሴቶች በዘር፣ ወይም በሃይማኖት ልዩነት ሳይደረግባቸው የማግባትና ቤተሰብ የመመስረት መብት አላቸው፡፡ በጋብቻ

አፈጻጸም፣ በጋብቻው ዘመንና በፍቺ ጊዜ እኩል መብት አላቸው፡፡ በፍቺም ጊዜ የልጆችን መብትና ጥቅም እንዲከበር የሚያደርጉ ድንጋጌዎች ይደነገጋሉ፡፡

2. ጋብቻ በተጋቢዎች ነጻና ሙሉ ፈቃድ ላይ ብቻ ይመሰረታል፡፡
3. ቤተሰብ የኅብረተሰብ የተፈጥሮ መሰረታዊ መነሻ ነው፡፡ ከኅብረተሰብና ከመንግሥት ጥበቃ የማግኘት መብት አለው፡፡
4. በሕግ በተለይ በሚዘረዘረው መሰረት በሃይማኖት፣ በባሕል የሕግ ሥርዓቶች ላይ ተመስርተው ለሚፈጸሙ ጋብቻዎች እውቅና የሚሰጥ ሕግ ሊወጣ ይችላል፡፡
5. የግል እና የቤተሰብ ሕግን በተመለከተ በተከራካሪዎች ፈቃድ በሃይማኖቶች ወይም በባሕሎች ሕጐች መሰረት መዳኘትን አይከለክልም፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡
6. በሕገ ኢትዮጵያ ጋብቻ በ1 (በአንድ) ወንድና በ1 (በአንድ) ሴት መካከል የሚደረግ ጥምረት ብቻ ነው።
7. በሕገ- ኢትዮጵያ ጋብቻ ከ18 ዓመት ዕድሜ በታች መፈፀም በጥብቅ የተከለከለ ነው።

# አንቀጽ 36

# የሴቶች መብት

1) ሴቶች መብቶችና ጥበቃዎች ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው፡፡
2) ሴቶች በጋብቻ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው፡፡
3) ሴቶች በበታችነትና በልዩነት በመታየታቸው የደረሰባቸውን የታሪክ ቅርስ ከግምት ውስጥ በማስገባት ይህ ቅርስ እንዲታረምላቸው በተጨማሪ የድጋፍ እርምጃዎች ተጠቃሚ የመሆን መብት አላቸው፡፡ በዚህ በኩል የሚወሰዱት እርምጃዎች ዓላማ በፖለቲካዊ፣ በማኅበራዊና በኢኮኖሚያዊ መስኮች እንዲሁም በመንግሥት እና በግል ተቋሞች ውስጥ ሴቶች ከወንዶች ጋር በእኩልነት ተወዳዳሪና ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ እንዲቻል ልዩ ትኩረት ለመስጠት ነው፡፡
4) ሴቶች ከጐጂ ባሕል ተጽዕኖ የመላቀቅ መብታቸውን መንግሥት ማስከበር አለበት፡፡
5) ሴቶችን የሚጨቁኑ ወይም በአካላቸው ወይም በአዕምሮአቸው ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ሕጐች፣ ወጐችና ልማዶች የተከለከሉ ናቸው፡፡
6) ሴቶች የወሊድ ፈቃድ ከሙሉ የደመወዝ ክፍያ ጋር የማግኘት መብት አላቸው፡፡ የወሊድ ፈቃድ ርዝመት ሴቷ የምትሠራውን ሥራ ሁኔታ፣ የሴቷን ጤንነት፣ የሕጻኑንና የቤተሰቡን ደህንነት ከግምት ውስጥ በማስገባት በሕግ ይወሰናል፡፡

7) በሕገ ኢትዮጵያ ሴት ልጅ ጠለፋ፣ አስገድዶ መድፈር፣  ፈጽሞ የተከለከለ የፌዴራል ሕግ ወንጀል ነው።
8)  ሴቶች የወሊድ ፈቃድ በሕግ በሚወሰነው መሰረት ከሙሉ የደመወዝ ክፍያ ጋር የሚሰጥ የእርግዝና ፈቃድን ሊጨምር ይችላል፡፡
9) ሴቶች በብሔራዊ የልማት ፖሊሲዎች ዕቅድና በፕሮጀክቶች ዝግጅትና አፈጻጸም፣ በተለይ የሴቶችን ጥቅም በሚነኩ ፕሮጀክቶች ሐሳባቸውን በተሟላ ሁኔታ እንዲሰጠ የመጠየቅ መብት አላቸው፡፡
10) **በሕገ-ኢትዮጵያ የሴት ልጅ ግርዛት** በጥብቅ የተከለከለ ነው።
11) **ሕገ-ኢትዮጵያን በመጣስ ሴት ልጁን ደብቆ ገርዞ የተገኘ ሰው በ 3 አመት እስራትና 5 ሺህ** የብር ቅጣት ይፈጸምበታል።
12) ሴቶች ንብረት የማፍራት፣ የማስተዳደር፣ የመቆጣጠር፣ የመጠቀምና የማስተላለፍ መብት አላቸው፡፡ በተለይም መሬትን በመጠቀም፣ በማስተላለፍ፣ በማስተዳደርና በመቆጣጠር ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው፡፡ እንዲሁም ውርስን በሚመለከት በእኩልነት የመታየት መብት አላቸው፡፡ ሴቶች የቅጥር፣ የሥራ እድገት፣ የእኩል ክፍያና ጡረታን የማስተላለፍ እኩል መብት አላቸው፡፡
13) ሴቶች በእርግዝናና በወሊድ ምክንያት የሚደርስባቸውን ጉዳት ለመከላከልና ጤንነታቸውን ለማስጠበቅ የሚያስችል የቤተሰብ ምጣኔ ትምህርት፣ መረጃ እና አቅም የማግኘት መብት አላቸው፡፡

# አንቀጽ 37

# የሕፃናት መብት

ማንኛውም ሕጻን የሚከተሉት መብቶች አሉት፤

ሀ/ በሕይወት የመኖር፣

ለ/ ስምና ዜግነት የማግኘት፣

ሐ/ ወላጆቹን ወይም በሕግ የማሳደግ መብት ያላቸውን ሰዎች የማወቅና የእነሱንም እንክብካቤ የማግኘት፣

መ/ ጉልበቱን ከሚበዘብዙ ልማዶች የመጠበቅ፣ በትምህርት½ በጤናውና በደህንነቱ ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ሥራዎች እንዲሠራ ያለመገደድ ወይም ከመሥራት የመጠበቅ፣

ሠ/ በትምህርት ቤቶች ወይም በሕጻናት ማሳደጊያ ተቋሞች ውስጥ በአካሉ ከሚፈጸም ወይም ከጭካኔና ኢሰብዓዊ ከሆነ ቅጣት ነጻ የመሆን፡፡

ሕጻናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ በመንግሥታዊ ወይም በግል የበጐ አድራጐት ተቋሞች፣ በፍርድ ቤቶች፣ በአስተዳደር ባለሥልጣኖች ወይም በሕግ አውጪ አካላት የሕጻናት ደህንነት በቀደምትነት መታሰብ አለበት፡፡
ወጣት አጥፊዎች፣ በማረሚያ ወይም በመቋቋሚያ ተቋሞች የሚገኙ፣ በመንግሥት እርዳታ የሚያድጉ ወጣቶች፣ በመንግሥት ወይም በግል እጓለ ማውታን ተቋሞች ውስጥ የሚገኙ መጣቶች ከአወቂዎች ተለይተው መያዝ አለባቸው፡፡
ከጋብቻ ውጭ የተወለዱ ሕጻናት በጋብቻ ከተወለዱ ሕጻናት ጋር እኩል መብት አላቸው፡፡ መንግሥት ለአካለ ስንኩላን ልዩ ጥበቃ ያደርግላቸዋል፡፡ በጉዲፈቻ የሚያድጉበትን ሥርዓት የሚያመቻቹና የሚያስፋፉ እንዲሁም ደህንነታቸውን፣ ትምህርታቸውን የሚያራምዱ ተቋሞች እንዲመሰረቱ ያበረታታል፡፡

# አንቀጽ 38

# ፍትሕ የማግኘት መብት

ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው፡፡
ሀ/ ማንኛውም ማኅበር የአባላቱን የጋራ ወይም የግል ጥቅም በመወከል፣

ለ/ ማንኛውም ቡድን ወይም ተመሳሳይ ጥቅም ያላቸውን ሰዎች የሚወክል ግለሰብ ወይም የቡድን አባል የመጠየቅና የማግኘት መብት አለው፡፡

# አንቀጽ 39

# የመምረጥና የመመረጥ መብት

በሕገ-ኢትዮጵያ በዘር ሥም መደራጀት፣ የፌደራል መንግሥት ወንጀል ነው።

በሕገ-ኢትዮድያ፤ በአገራችን በኢትዮድያ ውስጥ 3 (ሦስት) ቋሚ የሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች ብቻ እንዲኖሩ ይፈቅዳል። እነዚህ ፓርቲዎች መሪያቸውን በየ 4 ዓመት ይመርጣሉ።

እነዚህ ፓርቲዎች: ስማቸው እንደሚከተለው ተደንግጓል።

1) **ሕዝባዊ ፓርት (ሕፓ)**
2) **ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ዴፓ)**
3) **ፌዴራል ፓርቲ (ፌፓ) ናቸው።**

በሕገ- ኢትዮድያ መሰረት ለፕሬዚዴንትነት ለመወዳደር የሚችሉት ግለሰቦች

የብሔር፤ የጎሳ፤ ስም በመጠቀም ለመፎካከር አይችሉም። ለምሳሌ አማራ ኦሮሞ ጋምቤላ ወይም አጋዴን ወዘተ...

በሕገ-ኢትዮጵያ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በቀለም፣ በዘር፣ በጾታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ ወይም በሌላ አመለካከት ወይም በሌላ አቋም ላይ የተመሰረተ ልዩነት ሳይደረግበት የሚከተሉት **የመምረጥና የመመረጥ** መብቶች አሉት፤

ሀ/ በቀጥታ እና በነጻነት በመረጣቸው ተወካዮች አማካኝነት በሕዝብ ጉዳይ አስተዳደር

የመሳተፍ፣

ለ/ ዕድማው 18 ዓመት ሲሞላ በሕግ መሰረት የመምረጥ ፣

ሐ/ በማናቸውም የመንግሥት ደረጃ በየጊዜው በሚካሄድ ምርጫ የመምረጥና የመመረጥ፡፡ ምርጫው ሁሉን አቀፍ፣ በሁሉም እኩልነት ላይ የተመሰረተና በሚስጥር ድምጽ አሰጣጥ መራጩ ፈቃዱን በነጻነት የሚገልጽበት ዋስትና የሚሰጥ መሆን አለበት፡፡

በፖለቲካ ድርጅቶች፣ በሠራተኞች፣ በንግድ፣ በአሠሪዎችና በሙያ ማኅበራት ለተሳትፎ ድርጅቱ የሚጠይቀውን ጠቅላላና ልዩ የአባልነት መስፈርት የሚያሟላ ማንኛውም ሰው በፍላጐቱ አባል የመሆን መብቱ የተከበረ መሆን አለበት፡፡
በዚህ አንቀጽ በተመለከቱት ድርጅቶች ውስጥ ለኃላፊነት ቦታዎች የሚካሄዱ ምርጫዎች ነጻና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ይፈጸማሉ፡፡

# አንቀጽ 40

## የንብረት መብት

## በኢትዮጵያ ውስጥ ሀገር የጋራ ነው፣ ሃይማኖት የግል ነው።

1) ማንኛውም የኢትዮጵያ ዜጋ የግል ንብረት ባለቤት መሆኑ/መሆኗ ይከበርለታል/ ይከበርላታል፡፡ ይህ መብት የሕዝብን ጥቅም ለመጠበቅ በሌላ ሁኔታ በሕግ እስካልተወሰነ ድረስ ንብረት የመያዝና በንብረት የመጠቀም ወይም የሌሎችን ዜጐች መብቶች እስካልተቃረነ ድረስ ንብረትን የማፍራት የመሸጥ የማውረስ ወይም በሌላ መንገድ የማስተላለፍ መብቶችን ያካትታል፡፡

   ለዚህ አንቀጽ ዓላማ «የግል ንብረት» ማለት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ወይም ሕጋዊ ሰውነት በሕግ የተሰጣቸው ማኅበራት ወይም አግባብ ባላቸው ሁኔታዎች በሕግ በተለየ በጋራ የንብረት ባለቤት እንዲሆኑ የተፈቀደላቸው ማኅበረሰቦች በጉልበታቸው፣ በመፍጠር ችሎታቸው ወይም በካፒታላቸው ያፈሩት ተጨባጭ የሆነና የተጨባጭነት ጠባይ ሳይኖረው ዋጋ ያለው ውጤት ነው፡፡
2) የመንግሥት የመሬት ሞኖፖሊ በህግ የተከለከለ ይሆናል። የመንግሥት የመሬት ሞኖፖሊ ወደግለሰብ የመሬት ባለቤትነት፤ እንዳስፈላጊነቱ፤ የሚዛወርበት መንገድ በህግ ይደነገጋል። ሕጉን በሥራ ላይ የሚያውል መንግሥታዊ ድርጅት ይቋቋማል። ማንኛውም የመሬት ባለቤት መሬቱን በፈለገው መንገድ የማልማት፤ የማስያዝ፤ የመሸጥና የመለወጥ መብት አለው። በተዘዋዋሪ የግጦሽ መሬት ከብት እያረቡ የሚኖሩ፤ ስፍራው በተወሰነ ወደ ዘመናዊ የከብት እርባታ ኢኮኖሚ እንዲሸጋገሩ ይደረጋል።
3) በሕገ-ኢትዮጵያ መሠረት የገጠር መሬት በ13ቱ ክፍለ ሀገራት ውስጥ ለአራሽና ለአራሽ የገበሬ ማህበር ብቻ ይደለደላል።
4) ማንኛውም የትግራይ ነፃ አውጭ (TPLF) ድርጅት ወይም የኢሕአዴግ መንግሥት ከውጭም ሆነ በአገር ውስጥ ከግለሰቦችም ሆነ ከድርጅት ጋር ያደረጋቸውን የመሬት ሆነ ሌላም ማንኛውም ስምምንቶች እንዲሁም ስለገጠር መሬት ኪራይ በሚመለከት ውሎች በሙሉ ውድቅ ናቸው።

# አንቀጽ 41

## የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የባሕል መብቶች

1) **የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በመንግሥት ቁጥጥር ሥር የሚመራ ሳይሆን፤ በነፃ ገበያ ላይ የተመሠረተ ይሆናል። እንዳስፈላጊነቱ፤ መንግሥት የገበያ ኢኮኖሚውን ማረሚያ ፖሊሲዎች ማውጣት ይችላል። ነገር ግን ጤፍ በኩንታል፣ ጋዝ በሊትር፣ በቆሎ በኩንታል፣ ሥጋ በኪሎ፣ ወተት በሊትር እና ዘይት በሊትር ፣ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ዓቅም ጋር በማመዛዘን የዋጋ ተመን ማውጣት የሚችል የኢትዮጵያ የሕዝብ ምክር ቤት ብቻ ነው።**
2) ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በሀገሪቱ ውስጥ በማንኛውም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የመሰማራትና ለመተዳደሪያው የመረጠውን ሥራ የመሥራት መብት አለው፡፡
3) ሁሉም ኢትዮጵያዊ መተዳደሪያውን፣ ሥራውንና ሙያውን የመምረጥ መብት አለው፡፡
4) መንግሥት የጤና፣ የትምህርትና ሌሎች የማኅበራዊ አገልግሎቶችና የመሠረተ ልማት ሥራዎችን ያከናውናል።
5) መንግሥት የአካል እና የአዕምሮ ጉዳተኞችን፣ አረጋዊያንንና ያለ ወላጅ ወይም ያለ አሳዳጊ የቀሩ ሕጻናትን ለማቋቋምና ለመርዳት የሀገሪቱ የኢኮኖሚ አቅም በፈቀደው ደረጃ እንክብካቤ ያደርጋል፡፡
6) መንግሥት ለሥራ አጦችና ለችግረኞች ሥራ ለመፍጠር የሚያስችል ፖሊሲና ፕሮግራሞች ያወጣል።
7) የመንግሥት የመሬት ሞኖፖሊ በሕግ የተከለከለ ይሆናል። የመንግሥት የመሬት ሞኖፖሊ ወደግለሰብ የመሬት ባለቤትነት፤ እንዳስፈላጊነቱ፤ የሚዛወርበት መንገድ በሕግ ይደነገጋል። ሕጉን በሥራ ላይ የሚያውል መንግሥታዊ ድርጅት ይቋቋማል።
8) ማንኛውም የመሬት ባለቤት መሬቱን በፈለገው መንገድ የማልማት፤ የማስያዝ፤ የመሸጥና የመለወጥ መብት አለው።
9) በተዘዋዋሪ የግጦሽ መሬት ከብት እያረቡ የሚኖሩ፤ ስፍራው በተወሰነ ወደ ዘመናዊ የከብት እርባታ ኢኮኖሚ እንዲሸጋገሩ ይደረጋል።
10) መንግሥት የባሕልና ቋንቋዎች እንዲሁም የታሪክ ቅርሶችን የመንከባከብ በተጨማሪ ለሥነ ጥበብና ለስፖርት መስፋፋት አስተዋጽኦ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

## አንቀጽ 42 የሠራተኞች መብት

1) የፋብሪካና የአገልግሎት ሠራተኞች፣ ገበሬዎች፣ የእርሻ ሠራተኞች፣ ሌሎች የገጠር ሰራተኞች፣ ከተወሰነ ኃላፊነት ደረጃ በታች ያሉና የሥራ ጠባያቸው የሚፈቅድላቸው የመንግሥት ሠራተኞች የሥራና የኢኮኖሚ ሁኔታዎችን ለማሻሻል በማኅበር የመደራጀት መብት አላቸው፡፡ ይህ መብት የሠራተኛ ማኅበራትና ሌሎች ማኅበራትን የማደራጀት፣ ከአሠሪዎችና ጥቅማቸውን ከሚነኩ ሌሎች ድርጅቶች ጋር የመደራደር መብትን ያካትታል፡፡
2) የሠራተኛ ክፍሎች ሥራ ማቆምን ጨምሮ ቅሬታቸውን የማሰማት መብት አላቸው፡፡
3) እውቅና ባገኙት መብቶች ለመጠቀም የሚችሉት የመንግሥት ሠራተኞች በሕግ ይወሰናሉ፡፡
4) ሴቶች ሠራተኞች ለተመሳሳይ ሥራ ተመሳሳይ ክፍያ የማግኘት መብታቸው የተጠበቀ ነው፡፡ ሠራተኞች በአግባቡ የተወሰነ የሥራ ሰዓት ዕረፍት፣ የመዝናኛ ጊዜ፣ በየጊዜው ከክፍያ ጋር የሚሰጡ የዕረፍት ቀኖች፣ ደመወዝ የሚከፈልባቸው የሕዝብ በዓላት እንዲሁም ጤናማና አደጋ የማያደርስ የሥራ አካባቢ የማግኘት መብት አላቸው፡፡ እነዚህን መብቶች ተግባራዊ ለማድረግ የሚወጡ ሕጎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት እውቅና ያገኙትን መብቶች ሳይቀንሱ የተጠቀሱት ዓይነት የሠራተኛ ማኅበራት ስለሚቋቋሙበትና የጋራ ድርድር ስለሚካሄድበት ሥርዓት ይደነግጋሉ፡፡

## አንቀጽ 43 የልማት መብት

የኢትዮጵያ ሕዝብ በአጠቃላይም ሆነ በተናጠል የኑሮ ሁኔታውን የማሻሻልና የማያቋርጥ እድገት የማግኘት መብታቸው የተጠበቀ ነው፡፡
ዜጐች በብሔራዊ ልማት የመሳተፍ በተለይም አባል የሆኑበትን ማኅበረሰብ የሚመለከቱ ፖሊሲዎችና ፕሮጀክቶች ላይ ሐሳባቸውን እንዲሰጡ የመጠየቅ መብት አላቸው፡፡ መንግሥት በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚገባቸው ስምምነቶችም ሆኑ የሚያደርጋቸው ግንኙነቶች የኢትዮጵያን የማያቋርጥ እድገት መብት የሚያስከብሩ መሆን አለባቸው፡፡ የልማት እንቅስቀሴ ዋና ዓላማ የዜጐችን እድገትና መሰረታዊ ፍላጐቶች ማሟላት ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 44

## የአካባቢ ደህንነት መብት

1) ሁሉም ሰዎች ንፁህና ጤናማ በሆነ አካባቢ የመኖር መብት አላቸው፡፡
2) መንግሥት በሚያካሂዳቸው ኘሮግራሞች ምክንያት የተፈናቀሉ ወይም ኑሮአቸው የተነካባቸው ሰዎች ሁሉ በመንግሥት በቂ እርዳታ ወደ ሌላ አካባቢ መዘዋወርን ጨምሮ ተመጣጣኝ የሆነ የገንዘብ ወይም ሌላ አማራጭ ማካካሻ የማግኘት መብት አላቸው፡፡
3) የነዋሪውን ሕዝብ፣ የፋብሪካና የምርት ሰራተኛውንና በአጠቃላይ አከባቢውን ለውድመትና ለጉዳት በሚዳርጉ የሥራ ዘርፎችና ተቋማት ላይ ያተኮረ መመሪያና ለእነዚህ ጎጂ ውጤቶች መንስኤ ሊሆኑ የሚችሉትን እንቅስቃሴዎችና ተቋማት በሕግ መከልከል ይኖርበታል። ለጊዜያዊ ጥቅም ሲባል የአሁኑንና የወደፊቱን ትውልድና አካባቢ ደህንነት ለአደጋ ማጋለጥ ትክክል አይደለም። ስለሆነም አሁን በአገራችን የተከሰተው በኬሚካል የተበከለን ከባቢ፣ ወንዝና ጅረት ማጽዳት ያስፈልጋል።
4) የአካባቢና የወንዞች ወይንም የደኖች አያያዝን በተመለከተ ሃላፊነት የሚሰማው ዜጋን ለመፍጠር በአካባቢው አስተዳደርና በፌደራል አስተዳደር ሕግና ደንብ መሠረት ጥብቅ አስተዳደርና ቁጥጥር ይካሄዳል።

# አንቀጽ 45

ኢትዮጵያ ለሁሉም ዜጋ ዕኩል መብት በመስጠት የምታስተዳደር አገር ናት ። ሠራተኞች በአግባቡ የተወሰነ የሥራ ሰዓት ዕረፍት፣ የመዝናኛ ጊዜ፣ በየጊዜው ከክፍያ ጋር የሚሰጡ የዕረፍት ቀኖች፣ ደመወዝ የሚከፈልባቸው የሕዝብ በዓላት እንዲሁም ጤናማና አደጋ የማያደርስ የሥራ አካባቢ የማግኘት መብት አላቸው፡፡

እነዚህን መብቶች ተግባራዊ ለማድረግ የሚወጡ ሕጐች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት እውቅና ያገኙትን መብቶች ሳይቀንሱ የተጠቀሱት ዓይነት የሠራተኛ ማኅበራት ስለሚቋቋሙበትና የጋራ ድርድር ስለሚካሄድበት ሥርዓት ይደነግጋሉ፡፡

# አንቀጽ 46

13ቱ የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገሮች በቅርበት ሁሉም ዕኩልና በቂ የመንግስት አገልግሎትና ድጋፍ እንዲያገኙ የአስተዳደር ወሰን መሰረት የተቀመጡ ናቸው።

# አንቀጽ 47

13ቱ የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገሮች እና ዋና ከተሞቻቸው የስም ዝርዝር እንደሚከተለው ይሆናል።

1) አርሲ ክፍለ ሀገር .................................. አሰላ

2) ባሌ ክፍለ ሀገር...................................... ጐባ

3) ጋሞጎፋ ክፍለ ሀገር .............................. አርባ ምንጭ

4) በጌምድር ክፍለ ሀገር ....................................ጎንደር

5) ጎጃም ክፍለ ሀገር .................................. ደብረማርቆስ

6) ሐረርጌ ክፍለ ሀገር .............................. ሐረር

7) ኢሉባቦር ክፍለ ሀገር ........................... መቱ

8) ከፋ ክፍለ ሀገር .................................... ጂማ

9) ሸዋ ክፍለ ሀገር .................................. አዲስ አበባ

10) ሲዳሞ ክፍለ ሀገር ............................ ሐዋሳ

11) ትግራይ ክፍለ ሀገር ....................... መቀሌ

12) ወሊጋ ክፍለ ሀገር ........................... ነቀምት

13) ወሎ ክፍለ ሀገር ....................... ደሴ ናቸው ።

እንዲሁም

የአዲስ አበባ አስተዳደር ..............................አዲስ አበባ

የአፋር አስተዳደር ..........................................አሰብ

የጋምቤላ አስተዳደር .................................... ጋምቤላ

የኦጋደን አስተዳደር .............................. ጂጂጋ ናቸው ።

14) አስተዳደር ከክፍላተ ሀገር ጋር ዕኩል ሆኖ ተጠሪነታቸው ለፌደራል መንግሥት ነው።




## ታሪካዊ የኢትዮጵያ ክፍላተ ሀገራት መልከዓ ምድራዊ የአስተዳደር ካርታ

# አንቀጽ 48

13ቱ ክፍለ ሀገሮች ዕኩል በሆነ በሕዝባቸው ብዛት የአገሪቱን ድርሻ ተካፋዮች ናቸው።

# አንቀጽ 49

፩) የ13ቱ ክፍላተ ሀገሮች ዋና ከተማቸው አዲስ አበባ ትሆናለች።

፪) የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳር ተጠሪነቱ ለፌዴራል መንግስት ሆኖ ራሱን በራሱ

የማስተዳደር ስልጣን አለው።

# ስለ ኢትዮጵያ ዕይታ

ኢትዮጵያ በሰሜን ምስራቅ የአፍሪካ ቀንድ በመባል በሚታወቀው አካባቢ የምትገኝ ከአፍሪካ በቆዳ ስፋቷ ዘጠነኛ ደረጃ ላይ የምትገኝ አገር ናት፡፡ ዙሪያዋን አምስት አገሮች ያዋስኗታል፡፡ በምስራቅ በኩል ጅቡቲና ሶማሊያ፤ በሰሜንና በሰሜን ምስራቅ ቀይ ባሕር ፤ በደቡብ ኬንያ እና በምእራብ ሱዳን ናቸው፡፡ ጠቅላላ የቆዳ ሰፋት 1.1 ሚሊዬን ካሬ በላይ ሲሆን በውስጧ 7000 ኪ.ሜ የሚደርስ ርዝማኔ ያላቸው አስር ትላልቅ ወንዞችና ወደ 7000 ካሬ ጠቅላላ ስፋት ያላቸው ሀይቆች አሏት፡፡

**መልከዓ ምድር**

ኢትዮጵያ በውስጧ የተለያዩ መልከዓ ምድር ያላት አገር ከመሆኗ በተጨማሪ የአየር ንብረት አፈር የእንስሳትና የዕፅዋት ስብጥር የሚስተዋልባት አገር ናት፡፡ ኢትዮጵያ በጣም ከፍተኛ የሆኑ ተራሮች ከላያቸው ጠፍጣፋ የሆኑ አምባ የሚባሉ ፕላቶዎች ስምጥ የሆኑ ሸለቆዎች፤ ጥልቅ የወንዝ ሸለቆዎችና ሰፋፊ ሜዳዎች በውስጧ ይዛለች፡፡ ከባህር ጠለል በላይ 4620 ሜትር ከሚደርሰው ዳሽን ተራራ እስከ 148 ሜትር ከባህር ጠለል በታች እስከሆነው የዳሎል ዲፕረሽን ድረስ የሚሆን ልዩነት ያለው የከፍታና ዝቅታን የምታስተናግድ አገር ናት።

ለም ከሆኑ መሬቶችና ተራሮች አንስቶ ምንም የማይታይባቸው ከሚመስሉ ደልዳላ መሬቶች፣ ኢትዮጵያ ብዙ ትላልቅ እንደ አባይ፣ ተከዜ፣ አዋሽ፣ አሞ፣ ዋቢ፣ ሸበሌና ባሮ- አካቦ የመሳሰሉ ወንዞችና ገባሮች የታደለች አገር ናት፡፡

ከሜዲትራንያን ምስራቃዊ መጨረሻ ተነስቶ፣ ደቡብ ምስራቅ አፍሪካ የምትገኘው ሞዛምቢክ ድረስ የሚደርሰው ታላቁ ስምጥ ሸለቆ ኢትዮጵያን ለሁለት ከፍሏት ያልፋል፡፡

## የአየር ንብረት

ኢትዮጵያ እንደ መልከዓ ምድራዊ አቀማመጧ የአየር ንብረቷም በተለያዩ ቦታዎች የተለያየ ሁኔታ ይታዩባታል፡፡ መካከለኛው ኘላቶ አካባቢ ብዙም የማይፈራረቅ ወይና ደጋማ አይነት የአየር ንብረት ይታይበታል፡፡ ዝቅተኛው የአየር ንብረት በአማካኝ $6^0c$ ሲሆን ነገር ግን ወደ ቀይ ባህር በረሀ አካባቢ $60^0c$ የሚደርስባቸው ጊዜዎች አሉ፡፡ በብዙ የአገሪቱ አካባቢ በክረምት ወራት ይኸውም ሰኔ፣ ሀምሌና ነሀሴ ውስጥ ከፍተኛ የዝናብ መጠን ይመዘገባል፡፡

# የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር

የኢትዮጵያ (እንዲሁም በኤርትራ አብያተ ክርስትያናት) ዋና ካሌንደር ነው። አዲስ ዓመት በጁሊያን ካሌንደር አቆጣጠር በኦገስት 29 ወይም 30 የሚጀምር ሲሆን በግሪጎሪያን ካሌንደር ደግሞ ከ1901 እ.ኤ.አ. እስከ 2099 እ.ኤ.አ. ድረስ በሴፕቴምበር 11 ወይም 12 ይጀምራል። በየአራት ዓመቱ አንድ ቀን ይጨመራል። በአንድ ዓመት ውስጥ አስራ-ሁለት ባለ-ሠላሣ ቀናት እና አንድ ባለአምስት (ስድስት በአራት ዓመት አንዴ) ቀናት ያሉባቸው ወራት አሉ።

የዓመተ ምህረት ዘመናት ከጎርጎርዮስ 'አኖዶሚኒ' በ7 ወይም 8 አመታት የሚለይበት ምክንያት፣ ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት 400 አመት ያህል በኋላ አኒያኖስ እስክንድራዊ ዘመኑን ሲቆጥረው ትስብዕቱ በመጋቢት 29 1 ዓ.ም. እንደሆነ ስለገመተ ይህ በ*ትስብዕት ዘመን* 1ኛ አመት ሆኗል። ይህ አቆጣጠር በምሥራቅ ክርስቲያን አገራት ከተቀበለ በኋላም በ443 ዓ.ም. ከሮማ ፓፓና ከምሥራቅ አቡናዎች መካከል ልዩነት ደርሶባቸው፤ በ517 ሌላ መነኩሴ ዲዮኒሲዮስ ኤክሲጉዎስ ሌላ አቆጣጠር (*አኖዶሚኒ*) አቀረበ። በሱ ግምት ትስብዕቱ የተከሠተበት ቀን ከአኒያኖስ ግምት በፊት በ8 አመታት አስቀደመው። የ*አኖዶሚኒ* አቆጣጠር በምዕራብ አውሮፓ ላይኞነት በማግኘቱ የትስብእት ዘመን 1 አመተ ምህረት በ*አኖዶሚኒ* 9 እ.ኤ.አ. ሆነ። የኢትዮጵያ ዘመን ኣቆጣጠር የጁልያን ዘመን ኣቆጣጠር አይደለም።

# ወራት

| አማርኛ | ጎርጎርዮስ | በሰግርዓመት |
|---|---|---|
| መስከረም | ሴፕቴምበር11 | ሴፕቴምበር12 |
| ጥቅምት | ኦክቶበር11 | ኦክቶበር12 |
| ኅዳር | ኖቨምበር10 | ኖቨምበር11 |
| ታኅሣሥ | ዲሴምበር10 | ዲሴምበር11 |
| ጥር | ጃንዋሪ9 | ጃንዋሪ10 |
| የካቲት | ፌብርዋሪ8 | ፌብርዋሪ9 |
| መጋቢት | ማርች10 | ማርች10 |
| ሚያዝያ | ኤፕሪል9 | ኤፕሪል9 |
| ግንቦት | ሜይ9 | ሜይ9 |
| ሰኔ | ጁን8 | ጁን8 |
| ሐምሌ | ጁላይ8 | ጁላይ8 |
| ነሐሴ | ኦገስት7 | ኦገስት7 |
| ጳጉሜን | ሴፕቴምበር6 | ሴፕቴምበር6 |

# የኢትዮጵያ መልክዓ ምድር

ኢትዮጵያ በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ከ3-14 ዲግሪ ሰሜን እና ከ33-48 ዲግሪ ምሥራቅ የምትገኝ አገር ስትሆን የቆዳ ስፋቱዋም 1,127,127 ካሬ ኪ.ሜ. ነው። በሰሜን ከኤርትራ፣ በምዕራብ ከሱዳን፣ በደቡብ ከኬንያ፣ እንዲሁም በምሥራቅ ከጅቡቲ እና ከሶማሊያ ጋር ትዋሰናለች። የኢትዮጵያ አብዛኛው ግዛት በተራሮችና በሀይቆች የተሞላ ሲሆን፣ ታላቁ የምሥራቅ አፍሪካ ስምጥ ሸለቆ እነዚህኑ ከፍተኛ ቦታዎች ከሰሜን ምሥራቅ ወደ ደቡብ ምዕራብ በመጋደም ለሁለት ይከፍላቸዋል። በስምጥ ሸለቆው ዙሪያም በረሃማ የሆኑ ዝቅተኛ ቦታዎች ይገኛሉ። ይህንን መሰሉ የመልክዓ-ምድር ልዩነት አገሪቷ የተለያዩ የአየር ንብረት፣ የአፈር፣ የዕፅዋት እና የሕዝብ አሰፋፈር ገጽታዎች እንዲኖራት አስችሏታል። በከፍታና በመልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ የተነሣ በኢትዮጵያ ውስጥ ሦስት ዐይነት የአየር-ንብረት ክልሎች ይገኛሉ። እነሱም: ደጋ - ከፍታቸው ከባሕር ጠለል 2400 ሜትር የሚጀምር እና የሙቀት መጠናቸው ከ 16 ዲግሪ ሴ.ግ የማይበልጥ፤ ወይናደጋ - ከፍታቸው ከባሕር ጠለል ከ1500 እስከ 2400 ሜትር፣ ሙቀታቸውም ከ16 ዲግሪ ሴ.ግ እስከ 30 ዲግሪ ሴ.ግ የሚደርስና፣ ቆላ - ከባህር ጠለል በታች ጀምሮ እስከ 1500 ሜትር ከፍታ ያላቸው፣ የሙቀት መጠናቸውም ከ30 ዲግሪ ሴ.ግ እስከ 50 ዲግሪ ሴ.ግ የሚደርስ አከባቢዎች ናቸው። ዋናው የዝናብ ወቅት ከሰኔ አጋማሽ እስከ መስከረም አጋማሽ ሲሆን፣ ከሱ ቀደም ብሎ አልፎ አልፎ የሚጥል የበልግ ዝናብ በየካቲት እና በመጋቢት ይከሰታል። የተቀሩት ወራት በአብዛኛው ደረቅ ናቸው።

# አንቀጽ 50 የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

1) የኢትዮጵያ ሕዝብ ምክር ቤት በኢትዮጵያ ውስጥ ከማዕከላዊ መንግስት ጋር ዕኩል ስልጣን ያለው የፌዴራል መንግስት ነው።

2) በሕገ-ኢትዮጵያ መሰረት ሁሉም የሕዝብ ተወካዮች በሕዝቡ ለ4 ዓመት በአጠቃላይ አገራዊ ምርጫ ይመረጣሉ። እነሱም ከ**ሕዝባዊ** ወይም ከ**ዴሞክራትክ** ፓርቲ **ወይም ከፌዴራል ፓርቲ** የተወጣጡ ብቻ ናቸው።

3) እየአንዳንዱ ክፍለ ሀገር **3 ሴነተሮች እና እየአንዳንዱ አውራጃ 1 ተወካይ** መርጦ ወደ አዲስ አበባ ለ4 ዓመት መላክ አለባቸው። **13ቱም** ክፍለ ሀገር 3 ሴናተሮችን እና **አንድ**

ከየአውራጃዎች የተመረጡ ተውካዮችን መርጠው ለ4 ዓመት መላክ አለባቸው። እንዲሁም አዲስ አበባ ከተማ እራሱን የቻለ 3 ሴናተሮችን መርጦ መላክ አለበት።

# ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችና ኤጀንሲዎች

1) የውጭው ጉዳይ ሚንስቴር
2. የትምህርት ሚኒስቴር
3. የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር
4. የንግድ ሚኒስቴር
5. የገንዘብ ሚኒስቴር
6. የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር
7. የግብርና ሚኒስቴር
8. የመከላከያ ሚኒስቴር
9. የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር
10. የፍትህ ሚኒስቴር
11. የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር
12. የአቅም ግንባታ ሚኒስቴር
13. የትራንስፖርት ሚኒስቴር
14. የመሰረተ ልማት ሚኒስቴር
15. የውሃ ሀብት ልማትሚኒስቴር
16. ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
17. የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር

18. የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር

19. የገቢዎች ሚኒስቴር

20. የሴቶች ጉዳይ ሚኒስቴር

21. የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር

**የመንግስት ኤጀንሲዎች እና ባለሥልጣን መስሪያ ቤቶች**

- የተወካዮች ምክር ቤት
- የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ
- የኢትዮጵያ ካርታ ሥራዎች ባለስልጣን
- የኢትዮጵያ የፐራይቬታይዜሽንና የሕዝብ ድርጅቶች ተቆጣጣሪ
- የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ
- የኢትዮጵያ መድን ድርጅት
- የኢትዮጵያ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኮሚሽን
- የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኤጀንሲ
- የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ማስፋፊያ ኤጀንሲ
- የኢትዮጵያ የባህር እና ትራንዚት አገልግሎት ተቋም
- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ
- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ
- የትራንስፖርት ኮንስትራክሽን ዲዛይን ድርጅት
- የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ
- የኢትዮጵያ አየር መንገድ
- የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት
- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን
- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን
- የብሔራዊ ቤተመዛግብት እና ቤተመጻህፍት ኤጀንሲ
- የኢትዮጵያ የውጭ ንግድ ማስፋፊያ ኤጀንሲ
- የኢትዮጵያ የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን
- የፌደራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን
- የኢትዮጵያ የግብርና ግብዓት ባለሥልጣን

# የሥልጣን አወቃቀር እና ክፍፍል

## አንቀጽ 51

## ስለ ሥልጣን አካላት አወቃቀር እና የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባላት

1. የፌዴሬሽን ምክር ቤት በፌዴራሉ መንግሥት የሚገኝ ሕዝብ የሚልኩዋቸው አባላት የሚወከሉበት ምክር ቤት ነው፡፡
2. አንዳንዱ ክፍለ ሀገር 3 **ሴነተሮችና** አንዳንዱ አውራጃ **አንድ ተወካይ** ይኖረዋል።
3. የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባላት አንዳንዱ ክፍለ ሀገር 3 **ሴነተሮችና** አንዳንዱ አውራጃ **አንድ ተወካይ** በየክፍለ ሀገሩ በቀጥታ በሕዝብ እንዲመረጡ በማድረግ በፌዴሬሽን ምክር ቤት አባል እንዲወከሉ ያደርጋሉ፡፡

## አንቀጽ 52

## የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

1. የክፍለ ሀገራት ምክርቤቱ በሕገ-ኢትዮጵያ ሥር ሕግን የመወሰን ሥልጣን ይኖረዋል፡፡
2. ሕገ ኢትዮጵያ ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔን ያደራጃል፡፡
3. በሕዝቦች በሚነሱ ጥያቄዎች መሰረት ይወሰናል፡፡
4. ሕገ ኢትዮጵያ በሕዝቦች እኩልነት ላይ የተመሰረተ አንድነት ሥር እንዲሰድና እንዲዳብር ያደርጋል፡፡
5. ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጋር በጣምራ የተሰጡትን ሥልጣኖች ያከናውናል፡፡
6. በክፍለ ሀገሮች ለሚነሱ አለመግባባቶች መፍትሄ ይፈልጋል፡፡
7. የክፍለ ሀገራትና የፌዴራሉ መንግሥት የጋራ ተብለው የተመደቡ ገቢዎች በሁለቱ መካከል የሚከፋፈሉበትን፤ እንዲሁም የፌዴራሉ መንግሥት ለክፍለ ሀገሮች ድጐማ የሚሰጥበትን ቀመር ይወስናል፡፡
8. በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሕግ ሊወጣላቸው የሚገቡ የፍትሐ-ብሔር ጉዳዮችን ይለያል።

9. ማንኛውም ክፍለ ሀገር ይህን የሕገ-ኢትዮጵያን ሥርዓት በመጣስ መንግሥታዊ ሥርዓቱን አደጋ ላይ የጣለ እንደሆነ የፌዴራሉ መንግሥት ጣልቃ እንዲገባ ያዛል፡፡
10. የምክርቤቱን የተለያዩ ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎች ያቋቁማል፡፡
11. ምክር ቤቱ የራሱን አፈ-ጉባዔና ምክትል አፈ-ጉባዔ ይመርጣል፤ የራሱን የሥራ አፈጻጸምና የውስጥ አስተዳደር ደንብ ያወጣል፡፡

# አንቀጽ 53

## የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባላት መብት

1. ማንኛውም የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት አባል በማናቸውም የምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ በሚሰጠው አስተያየት ወይም ድምጽ ምክንያት ያለ-መከሠስ መብቱ ይጠበቅለታል፤ አስተዳደራዊ እርምጃም አይወሰድበትም፡፡
2. ማንኛውም የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት አባል ከባድ ወንጀል ሲፈጽም እጅ ከፍንጅ ካልተያዘ በስተቀር ያለ-ምክር ቤቱ ፈቃድ አይያይዝም፤ በወንጀልም አይከሰስም፡፡

# አንቀጽ 54

## ውሳኔዎችና የሥነ-ሥርዓት ደንቦች

1. የሕዝብ ምክር ቤት ተወካዮች በፌዴራልም ሆነ በክፍለ ሀገራት ለ4 ዓመታት ሥራ አገልግሎት በቀጥታ በሕዝብ የተመረጡ ብቻ ናቸው።
2. የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት ምልዓተ ጉባዔ የሚኖረው ከአባላቱ ሁለት ሦስተኛው የተገኙ እንደሆነ ነው፡፡ ማናቸውም ውሳኔ የሚያልፈው በስብሰባ ላይ ከተገኙት የምክር ቤቱ አባላት ከግማሽ በላይ ድምጽ ሲደገፍ ብቻ ነው፡፡
3. አባላት ድምጽ መስጠት የሚችሉት በአካል ሲገኙ ብቻ ነው፡፡

# አንቀጽ 55 ስለበጀት

**የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት ቅዲሚያ የኢትዮጵያ ትንሳዔ የእርሻ አጠቃቀም ፕላን ለ13 ቱም ክፍለ ሀገራት ገበሬውን በማህበር በማደራጀት ለ13ቱም ክፍላተ ሀገር የግብርና ተዳዳሪዎች ማህበር ዕኩል በሆነ መልክ ፤**

1) **ትራክተር**

2) **ኮምባይነር**

3) **ሰው ሠራሽ የዝናብ መሣሪያ በማስገባት እጅግ አንገብጋቢና ዋና የኢትዮድያ ፌዴራል መንግስት የኢትዮጵያ ዕድገት የመነሻ መሠረት ድንጋይ መጣል አለበት።**

የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት በጀቱን ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በማቅረብ ያስወስናል፡፡

# አንቀጽ 56

## የምክር ቤቱ አፈጉባኤ ሥልጣን

1. የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ የምክር ቤቱን ስብሰባዎች ይመራል፡፡
2. ምክርቤቱን በመወከል ጠቅላላ የአስተዳደር ሥራዎችን ይመራል፡፡
3. ምክር ቤቱ በአባሎቹ ላይ የወሰነውን የዲስፕሊን እርምጃ ያስፈጽማል፡፡

# አንቀጽ 57

## ስብሰባና የሥራ ዘመን

1. የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ ይሰበሰባል፡፡
2. የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት የሥራ ዘመን 4 ዓመት ይሆናል፡፡

# አንቀጽ 58

## በሁለቱም ምክር ቤቶች አባል መሆን የማይቻል ስለመሆኑ

1) ማንኛውም ሰው በአንድ ጊዜ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት አባል ሊሆን አይችልም፡፡

# ስለሪፐብሊኩ ፕሬዚዴንት

# አንቀጽ 59

## ስለፕሬዚዴንቱ

**ፕሬዚዴንቱ** የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መሪ ነው፡፡

# አንቀጽ 60

# የፕሬዚዴንቱ አሰያየም

1. የኢትዮጵያ ፕሬዚዴንት በመስፈርቱ መሠረት በኢትዮጵያ ሕዝብ በ13ቱም ክፍለ ሀገራት ተወዳድሮ **አንድ ሰው አንድ ድምፅ መሠረት** (**one man one vote rule**) ያሸነፈ ወይም ያሸነፈች ሰው ይሆናል።
2. የፕሬዚዴንቱ የሥራ ዘመን 4 ዓመት ይሆናል፡፡ አንድ ሰው ከሁለት ጊዜ በላይ ለፕሬዚዴንትነት ሊመረጥ አይችልም።
3. የሪፐብሊኩ ፕሬዚዴንት ምርጫ ከጸደቀ በኋላ ሥራውን ከመጀመሩ በፊት የጋራ ስብሰባው በሚወስነው ጊዜ በስብሰባው ፊት **ለሕገ-ኢትዮጵያና ለኢትዮጵያ ሕዝብ** ያለውን ታማኝነት በሚቀጥሉት ቃላት በመሃላ ይገልጻል፡፡

**«እኔ.......በዛሬው ዕለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዴንት በመሆን ሥራዬን ስጀምር የተጣለብኝ ከፍተኛ ኃላፊነት በታማኝነተና በቅንነት ለመፈጸም ቃል እገባለሁ፡፡»**

# አንቀጽ 61

# የፕሬዚዴንቱ ሥልጣንና ተግባር

1. የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት እና የፌዴሬሽኑን ምክር ቤት ዓመታዊ የጋራ ስብሰበባ ይከፍታል፡፡
2. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያጸደቃቸውን ሕጐችና ዓለም አቀፍ ስምምነቶች በነጋሪትጋዜጣ ያውጃል፡፡
3. ሀገሪቷን በውጭ ሀገሮች የሚወክሉትን አምባሳደሮችና ሌሎች መልክተኞች ይሾማል፡፡
4. የውጭ ሀገር አምሳደሮችንና የልዩ መልዕክተኞችን የሹመት ደብዳቤ ይቀበላል፡፡
5. በሕግ መሰረት ኒሻኖችና ሽልማቶችን ይሰጣል፡፡
6. በሕግ በተወሰነው መሰረት ከፍተኛ የውትድርና ማዕረጐችን ይሰጣል፡፡
7. በሕግ መሰረት ይቅርታ ያደርጋል፡

## የሕግ አስፈጻሚ አካል

## አንቀጽ 62

## ስለ አስፈጻሚነት ሥልጣን

1. የኢትዮጵያ ፌዴራል መንግሥት ከፍተኛ የአስፈጻሚነት ሥልጣን የተሰጠው ከማዕከላዊ መንግስት ጋር ዕኩል ሥልጣን ያለው ነው፡፡

## አንቀጽ 63

# የኢትዮጵያ ፕሬዚዴንት ልዩ ሥልጣንና ተግባር

1) የሀገሪቱ ርዕሰ መስተዳድር፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሰብሳቢ ነው፡፡
2) የሚኒስትሮች ምክር ቤት አባሎችን ከሁለቱ ምክር ቤቶች አባላት ወይም ለሥራው ብቃት ካላቸው ሌሎች ግለሰቦች መካከል ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በእጩነት አቅርቦ ሹመታቸውን ያጸድቃል፡፡
3) የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚያወጣቸውን ሕጐች፣ ፖሊሲዎች፣ መመሪያዎችና ውሳኔዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፡፡
4) የሚኒስትሮች ምክር ቤትን ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይወክላል፡፡
5) የሚኒስትሮች ምክር ቤት ያወጣቸውን ፖሊሲዎች፣ ደንቦች መመሪያዎችና ውሳኔዎች ተፈጻሚነትን ይከተተላል፡፡
6) የሀገሪቱን የውጭ ፖሊሲ በበላይነት ያስፈጽማል፡፡
7) ኮሚሽነሮችን፣ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሹመታቸውን ያጸድቃል፡፡
8) የመስተዳድሩን ሥራ አፈጻጸምና ብቃት ይቆጣጠራል፣ አስፈላጊ የሆኑ የእርምት እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡
9) ከፍተኛ የመንግሥት ሲቪል ሹመቶችን ይሰጣል፡፡
10) የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚያወጣው ሕግ ወይም በሚሰጠው ውሳኔ መሠረት ኒሻኖችንና ሽልማቶችን ይሰጣል፡፡
11) ስለ ሀገሪቱ ሁኔታ፣ በመንግሥት ስለ ተከናወኑ ተግባራትና ስለ ወደ ፊት እቅዶች ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በየወቅቱ ሪፖረት ያቀርባል፡፡
12) በመንግሥትና በሌሎች ሕጐች የተሰጡትን ተግባሮች ያከናውናል፡፡
13) **ሕገ ኢትዮጵያን** ያከብራል፤ ያስከበራል፡፡

# አንቀጽ 64

# የሚኒስትሮች ምክር ቤት

1) የሚኒስትሮች ምክር ቤት፤ **ፕሬዚዴንትና ምክትል ፕሬዚዴንቱ** በሕግ በሚወሰን መሰረት ሌሎች አባሎች የሚገኙበት ምክር ቤት ነው፡፡

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለ**ፕሬዚዴንቱ** ነው፡፡
2. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለሚወስነው ውሳኔ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተጠሪ ነው፡፡

# አንቀጽ 65

# የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የወጡ ሕጎችና የተሰጡ ውሳኔዎችን በሥራ መተርጐማቸውን ያረጋግጣል፣ መመሪያዎችን ይሰጣል፡፡
2. የሚኒስትሮችንና በቀጥታ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ተጠሪ የሆኑ ሌሎች የመንግሥት አካላትን አደረጃጀት ይወስናል፣ ሥራቸውን ያስተባብራል፣ ይመራል፡፡
3. የፌዴራሉን መንግሥት ዓመታዊ በጀት ያዘጋጃል፣ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲጸድቅም ተግባራዊነቱን ያረጋግጣል፡፡
4. የገንዘብና የፋይናንስ ፖሊሲን ተግባራዊነት ያረጋግጣል፣ ብሔራዊ ባንክን ያስተዳድራል፣ ገንዘብ ያትማል፣<br>ከሀገር ውስጥና ከውጭ ይበደራል፣ የውጭ ምንዛሪና የገንዘብ ልውውጥን ይቆጣጠራል፡
5. የፈጠራና የኪነ ጥበብ መብቶችን ያስጠብቃል፡፡
6. ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና የልማት ፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎችን ይነድፋል፣ ያስፈጽማል፡፡
7. አንድ ወጥ የመለኪያ ደረጃዎችና የጊዜ ቀመር ያወጣል፡፡
8. የሀገሪቱን የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ያወጣል፣ ያስፈጽማል፡፡
9. ሕግና ሥርዓት መከበሩን ያረጋግጣል፡፡ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ ያስጸድቃል፡፡

10. ጦርነት ጨምሮ በማናቸውም ጉዳዮች ላይ የሕግ ረቂቅ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀርባል፡፡
11. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል፡፡
12. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚሰጠው ሥልጣን መሠረት ደንቦችን ያወጣል፡

# አንቀጽ 66

# የውጭ ግንኙነት መርሆዎች

1. የኢትዮጵያን ሕዝብ ጥቅም የሚያስጠብቅና የሀገሪቱን ሉዓላዊነት የሚያስከብር የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ማራመድ፡፡
2. የመንግሥታትን ሉዓላዊነትና እኩልነት ማክበር፣ በሌሎች ሀገሮች ጉዳዮች ውስጥ ጣልቃ አለመግባት፡፡
3. የሀገሪቱ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ በጋራ ጥቅምና በእኩልነት ላይ የተመሰረተ መሆኑን እንዲሁም በዓለምአቀፍ ደረጃ የሚደረጉ ስምምነቶች የኢትዮጵያን ጥቅም የሚያስከብሩ መሆናቸውን ማረጋገጥ፡፡
4. የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት የሚያስከብሩና የሕዝቧን ጥቅም የማይጻረሩ ዓለም አቀፍ ሕጎችና ስምምነቶችን ማክበር፡፡
5. ከጎረቤት ሀገሮችና ከሌሎችም የአፍሪካ ሀገሮች ጋር በየጊዜው እያደገ የሚሄድ ኢኮኖሚያዊ ኅብረትና የሕዝቦች ወንድማማችነትን ማጐልበት፡፡
6. በሀገሮች መካከል የሚነሱ ግጭቶችን ሰላማዊ በሆነ መንገድ እንዲፈቱ ጥረት ማድረግ፡

# አንቀጽ 67

# የመከላከያ መርሆዎች

1. በሕገ  ኢትዮጵያ መሠረት የኢትዮጵያ ፕሬዚዴንት ሥልጣንና የመከላከያ ሰራዊት አገልግሎት መለያየት አለበት። ያ ማለት የኢትዮጵያ ፕሬዚዴንት እንደተለመደው የጠቅላይ ጦር አዛዥ መሆን አይችሉም ማለት ነው።

2. የሀገሪቱ የመከላከያ ሠራዊት ከአዲስ አበባ ጋር ከ14ቱ ክፍለ ሀገር ዕኩል በሆነ መልክ የተውጣጣ መሆን አለበት።

3. በሕገ ኢትዮጵያ መሠረት የኢትዮጵያ የመከላከያ ሚኒስትር ሆኖ የሚሾመው በሴናተሮችና በሕዝብ ተጠሪዎች ወለል አንድ ላይ (የሕዝብ ምክር ቤት) ከፍተኛ ውይይት ተደርጎ የተመረጠ ሲቪል መሆን አለበት።

4. የመከላከያ ሠራዊት የሀገሪቱን ሉዓላዊነት ከመጠበቅ በተጨማሪ በአስቸኳይ ጊዜ የሚሰጡትን ተግባሮች ያከናውናል፡፡

5. የመከላከያ ሠራዊቱ በማናቸውም ጊዜ **ለሕገ-ኢትዮድያ** ተገዢ ይሆናል፡፡

6. የመከላከያ ሠራዊቱ ተግባሩን ከፖለቲካ ድርጅቶች ወገናዊነት ነጻ በሆነ አኳኋን ያከናውናል፡፡ እንዲሁም የአገራችን ፌደራል ጦር አዲስ አበባን ጨምሮ ከየክፍለ ሀገር ዕኩል የተውጣጣ እንጂ በሕዝብ ብዛት እየተባለ የአንድ ጎሳ፣ ወገን አብላጫ ማድረግ ፈጽሞ የተከለከለ ነው።

7. በሕገ ኢትዮጵያ መሠረት በሕገወጥ መንገድ መሣሪያ መታጠቅ የተከለከለ ነው። ነገር ግን የፀጥታ ስጋት ያለባቸው አከባቢ ራሳቸውን ከአሸባሪዎች ለመጠበቅ በሕጋዊ ፈቃድ ለመጠቀም እንዲችሉ የየአከባቢ የሕዝብ ምክር ቤት መወሰን አለበት። ከዚያ ውጭ ሕገወጥ መሳሪያ ይዞ መገኘት በገንዘብና በእስራት የሚያስቀጣ ወንጀል ነው። ዝርዝሩ በሕዝብ ምክር ቤት በሕግ ይወሰናል።

8. በሕገ ኢትዮጵያ መሠረት አንድ ወገን ተነስቶ የኢትዮድያን ሕዝብ በብሔራቸው፣ በጎሳቸው፣ ምክንያት ለይቶ ከኖሩበት ስፍራ እንዲለቁ ተብለው ከቤት ንብረታቸው ማፈናቀል፣ የእምነት ተቋሞችን ማቃጠል፣ የንፁሀን ደም ማፍሰስ፣ እና ሰው መግደል ወንጀለኞቹ በሞት መቀጣት አለባቸው። የዚህ ወንጀል ክስ ምንጊዜም በይርጋ አይታገድም።

# አንቀጽ 68

# ፖለቲካ ነክ ዓላማዎች

1. መንግሥት በዴሞክራሲያዊ መርሆዎች ላይ በመመሥረት ሕዝቡ በሁሉም ደረጃዎች ራሱን በራሱ የሚያስተዳድርበትን ሁኔታ ማመቻቸት አለበት፡
2. የፌዴራል መንግሥት ተወካዮች በቁጥር በተወሰኑ ጉዳዮች በሚመለከት ከክፍለ ሀገር አስተዳደር ጋር በስምምነት ሊሰሩ ይችላሉ፣ ነገር ግን የፌዴራል መንግሥት ተወካዮች ያለክፍለ ሀገሩ ፈቃድ የፌዴራል መንግሥት በክፍለ ሀገር ጉዳይ ውስጥ እንዳይገባ ሕገ ኢትዮጵያ በጥብቅ ይከለክላል። እንዲሁም መንግሥት የሕዝብን ማንነት የማክበርና በዚሁ ላይ በመመርኮዝ በመካከላቸው እኩልነት፣ አንድነትና ወንድማማችነትን የማጠናከር ግዴታ አለበት፡፡
3. ኢትዮጵያ ለረጅም ዘመናት ዜጎቿን ያለአንዳች ልዩነት በየክፍለ ሀገራቸው አብረው ተከባብረው እንድንኖር ያደረገች አገር፣ አሁንም ለወደፊትም የምታደርግ አገር ናት።
4. የየክፍለ ሀገር ዋና አስተዳዳሪዎች፣ የፌደራል መንግስት ሥልጣን በየክፍለ ሀገር አስተዳደር ላይ በጣም ውስን መሆኑን ማወቅ አለባቸው።
5. እያንዳንዱ ክፍለ ሀገር የየክፍለ ሀገሩ ክብር ጠብቆ ራሱን በራሱ እያስተዳደረ መቀጠል አለበት።

# አንቀጽ 69

# ኢኮኖሚ ነክ ዓላማዎች

1. በሕገ ኢትዮጵያ የፌደራል መንግሥትንና የክፍላተ ሀገር መንግሥት አንድ ላይ ተቀራርበው ለአንድ አገር መሥራት አለባቸው። መንግሥት ሁሉም ኢትዮጵያውያን የሀገሪቱ የተጠራቀመ እውቀትና ሀብት ተጠቃሚዎች የሚሆኑበትን መንገድ የመቀየስ ኃላፊነት አለበት፡፡
2. የፌደራል መንግሥት በክፍለ ሀገር መንግስት ጋር የሥራ ትብብር ድርሻ ለመካፈል እንጅ የፌደራል መንግስት በክፍለ ሀገር ጉዳይ ላይ ጣልቃ እንዲገባ ሕገ ኢትዮጵያ አይፈቅድም። መንግሥት የኢትዮጵያውያንን የኢኮኖሚ ሁኔታዎች ለማሻሻል እኩል ዕድል እንዲኖራቸው ለማድረገና ሀብት ፍትሐዊ በሆነ መንገድ የሚከፋፈሉበትን ሁኔታ የማመቻቸት ግዴታ አለበት፡፡ የክፍለ ሀገር መሪዎች ግንኙነት ማጠናከር አለበት። የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ እንዳይደርስ መከላከልና አደጋው ሲደርስም ለተጐጂው እርዳታ በወቅቱ እንዲደርስ ማድረግ፡፡ በእድገት ወደኋላ ለቀሩ ሕዝቦች መንግሥት ልዩ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

3. የፌደራል መንግሥት በክፍላተ ሀገር ጉዳይ ላይ በስምምነት ለመረዳዳት ካልሆነ በስተቀር፣ ፌደራል በክፍለ ሀገር አስተዳደር ውስጥ ምንም ዓይነት ጣልቃ እንዳይገባ ሕገ ኢትዮድያ በጥብቅ ይገድባል። መንግሥት መሬትንና የተፈጥሮ ሀብትን በሕዝብ ሥም በይዞታው ሥር በማድረግ ለሕዝቡ የጋራ ጥቅምና እድገት እንዲውሉ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

4. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምክር (የሴነትና የሕዝብ ተጠሪዎች ወለል) የኢትዮድያ ክፍላተ ሀገር የገቢና የወጭ መዋቅር ለማውጣት አይችሉም። ነገር ግን የክፍላተ ሀገር መንግስት በነፃነት በሕገ ኢትዮጵያ ሥር የራሱን በክፍለ ሀገሩ ሕግ መሰረት የክፍለ ሀግሩን መዋቅር የማውጣት ሙሉ መብት አላቸው። የሀገር ልማት ፖሊሲዎችና ኘሮግራሞች በሚዘጋጁበት ወቅት መንግሥት ሕዝቡን በየደረጃው ማሳተፍ አለበት፡፡ የሕዝብንም የልማት እንቅስቃሴዎች መደገፍ አለበት፡፡

   የኢትዮጵያ የፌደራልና የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት ፍርድ ቤቶች የክፍላተ ሀገር ፍርድ ቤቶች ሕግና ደንብ በሕገ ኢትዮጵያ መሠረት መሆኑን ማጣራትና ማክበር አለባቸው። መንግሥት በሀገር ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ልማት እንቅስቃሴ ውስጥ ሴቶች ከወንዶች ጋር በእኩልነት የሚሳተፉበትን ሁኔታ የማመቻቸት ኃላፊነት አለበት፡፡

5. የኢትዮጵያ ክፍላተ ሀገር ለእድገትና ለብልፅግና ከፌደራል መንግስት ጋር ተቀናጅቶ የሚሠሩ ተግባራትን በጋራ እየሠሩ የራሳቸውን የክፍላተ ሀገር ተግባር ግን በራሳቸው በክፍለ ሀገሩ ሕግ መሠረት ብቻ የፌደራል መንግሥት ምንም ጣልቃ ሳይገባ መሥራት አለባቸው። መንግሥት የዜጎችን ጤንነት፣ ደህንነትና የኑሮ ደረጃ ለመጠበቅ መጣር አለበት፡፡

6. የኢትዮጵያ ክፍላተ ሀገር ማንኛውንም ከፌደራል መንግሥት የሚመጣ የገቢ ድርሻ እንደ አስፈላጊነቱ መጠቀም እንጂ በአንድ ቦታ ብቻ ገድበው መጠቀም የለባቸውም።

7. የኢትዮጵያ የፌደራል መንግሥት በክፍላተ ሀገርና በተለያዩ በክፍለ ሀገሩ ድርጅቶች ላይ ምንም ዓይነት ተፅዕኖ የማድረግ ሥልጣን የለውም።

# አንቀጽ 70

## ማኅበራዊ ነክ ዓላማዎች

1. የሀገሪቱ አቅም በፈቀደ መጠን ሁሉም ኢትዮጵያዊ የትምህርት፣ የጤና አገልግሎት፣ የንፁህ ውሃ፣ የመኖሪያ፣ የምግብና የማኅበራዊ ዋስትና እንዲኖረው ይደረጋል፡፡
2. ትምህርት በማናቸውም ረገድ ከሃይማኖት፣ ከፖለቲካ አመለካከቶች እና ከባሕላዊ ተፅእኖዎች ነጻ በሆነ መንገድ መካሔድ አለበት፡፡

# አንቀጽ 71

# ባሕል ነክ ዓላማዎች

1. መንግሥት መሰረታዊ መብቶችንና ሰብዓዊ ክብርን የማይቃረኑ ባሕሎችና ልማዶች በእኩልነት እንዲጐለብቱና እንዲያድጉ የመርዳት ኃላፊነት አለበት፡፡
2. የሀገር የተፈጥሮ ሀብቶችንና የታሪክ ቅርሶችን መጠበቅ የመንግሥትና የሁሉም ኢትዮጵያዊ ግዴታ ነው፡፡
3. መንግሥት አቅም በፈቀደ መጠን ኪነጥበብን፣ ሳይንስንና ቴክኖሎጂን የማስፋፋት ግዴታ አለበት፡፡

### አንቀጽ 72

### የአካባቢ ደህንነት ጥበቃ ዓላማዎች

1. መንግሥት ሁሉም ኢትዮጵያዊ ንጹሕና ጤናማ አካባቢ እንዲኖረው የመጣር ኃላፊነት አለበት፡
2. ማንኛውም የኢኮኖሚ ልማት እርምጃ የአካባቢውን ደህንነት የማያናጋ መሆን አለበት፡
3. የሕዝብን የአካባቢ ደህንነት የሚመለከት ፖሊሲና ኘሮግራም በሚነደፍበትና ሥራ ላይ በሚውልበት ጊዜ የሚመለከተው ሕዝብ ሁሉ ሐሳቡን እንዲገልጽ መደረግ አለበት፡፡
4. መንግሥትና ዜጐች አካባቢያቸውን የመንከባከብ ግዴታ አለባቸው፡፡

# አንቀጽ 73

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

# ስለ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ

1. ሀ/ የውጭ ወረራ ሲያጋጥም ወይም ሕግ ማስከበር ሥርዓት ለመቋቋም የማይቻል ሲሆን፣ ማናቸውም የተፈጥሮ አደጋ ሲያጋጥም ወይም የሕዝብን ጤንነት አደጋ ላይ የሚጥል በሽታ ሲከሰት፣ የፌዴራሉ መንግሥት የሚኒስትሮች ምክር ቤት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የመደንገግ ሥልጣን አለው፡፡

   ለ/ የተፈጥሮ አደጋ ሲያጋጥም ወይም የሕዝብን ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል በሽታ ሲከሰት **ክፍለ *ሀገራት*** የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ሊያውጁ ይችላሉ፡፡ ዝርዝሩ በመንግሥት ይወሰናል፡፡

2) የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሥራ ላይ ባለ ጊዜ የታወጀ ከሆነ በታወጀ በአርባ ስምንት ሰዓታት ውስጥ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መቅረብ አለበት። አዋጁ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሁለት ሦስተኛው ድምጽ ተቀባይነት ካላገኘ ወዲያውኑ ይሻራል፡፡

3) የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በሚታወጅበት ጊዜ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣቸው ደንቦች መሰረት የሀገርን ሰላምና ሕልውና፣ የሕዝብን ደህንነት፣ ሕግና ሥርዓትን የማስከበር ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

## አንቀጽ 74

## የፋይናንስ ወጪን በሚመለከት

1. የፌዴራሉ መንግሥትና **ክፍለ *ሀገራት*** በሕግ የተሰጧቸውን ኃላፊነቶችና ተግባሮች ለማከናወን የሚያስፈልጋቸውን ወጪ በየበኩላቸው ይሸፍናሉ፤ ሆኖም ማንኛውም በውክልና ለሚፈጽመው ተግባር የሚያስፈልገው ወጪ ሌላ ስምምነት ከሌለ በቀር ውክልናውን በሰጠው ወገን ይሸፈናል፡፡

2. የፌዴራሉ መንግሥት ለ**ክፍለ *ሀገራት*** የተመጣጠነ እድገት እንቅፋት ካልሆነ በስተቀር ለአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ፣ ለመልሶ መቋቋምና ለልማት ማስፋፊያ ብድርም ሆነ እርዳታ ሊሰጥ ይችላል፡፡ የፌዴራሉ መንግሥት ለ**ክፍለ *ሀገራት*** ለሚያስፈልጋቸው ወጪ የሚያደርገውን ድጐማ በሚመለከት ኦዲትና ቁጥጥር የማድረግ ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

# አንቀጽ 75

# የፋይናንስ ገቢን በሚመለከት

የፌዴራሉ መንግሥትና **ክፍለ ሀገራት** የሚዋቀረውን የፌዴራል አደረጃጀት የተከተለ የገቢ ክፍፍል ያደርጋሉ፡፡

# አንቀጽ 76

## የፌዴራል መንግሥት የታክስና  የግብር ሥልጣን

1. የፌዴራል መንግሥት በወጪና ገቢ ዕቃዎች ላይ የጉምሩክ ቀረጥ፣ የታክስና ሌሎች ክፍያዎች ይጥላል፣ ይሰበስባል፡፡
2. በፌዴራል መንግሥትና በዓለም አቀፍ ድርጅቶች ተቀጣሪዎች ላይ የሥራ ግብር ይጥላል፣ ይሰበስባል፡፡
3. በፌዴራል መንግሥት ባለቤትነት ሥር በሆኑ የልማት ድርጅቶች ላይ የንግድ ትርፍ ግብር፣ የሥራ ግብር፣ የሽያጭና የኤክሳይስ ታክስ ይጥላል፣ ይሰበስባል፡፡
4. በብሔራዊ የሎተሪ እና ሌሎች የዕድል ሙከራ ገቢዎች ላይ ታክስ ይጥላል፣ይሰበስባል፡፡
5. በአየር፣ በባቡርና በባሕር ትራንስፖርት ገቢዎች ላይ ታክስ ይጥላል፣ ይሰበስባል፡፡
6. በፌዴራል መንግሥት ባለቤትነት ሥር በሚገኙ ቤቶችና ሌሎች ንብረቶች ገቢ ላይ ግብር ይጥላል፣ ይሰበስባል፤ ኪራይ ይወስናል፡፡
7. የፌዴራል መንግሥት አካላት ከሚሰጧቸው ፈቃዶችና አገልግሎቶች የሚመነጩ ክፍያዎችን ይወስናል፣ ይሰበስባል፡፡
8. የሞኖፖል ታክስ ይጥላል፣ ይሰብሰባል፡፡
9. የፌዴራል የቴምብር ሽያጭ ቀረጥ ይጥላል፣ ይሰበስባል፡፡

# አንቀጽ 77

## ክፍለ ሀገራት የታክስና የግብር ሥልጣን

1. **ክፍለ *ሀገራት*** በድርጅት ተቀጣሪዎች ላይ የሥራ ግብር ይጥላሉ፣ ይሰበስባሉ፡፡
2. የመሬት መጠቀሚያ ክፍያ ይወስናሉ፣ ይሰበስባሉ፡፡
3. በግል የሚያርሱና በኅብረት ሥራ ማኅበራት በተደራጁ ገበሬዎች ላይ የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር ይጥላሉ፣ ይሰበስባሉ፡፡
4. በ**ክፍለ *ሀገራት*** በሚገኙ ግለሰብ ነጋዴዎች ላይ የንግድ ትርፍ ግብርና የሽያጭ ታክስ ይጥላሉ፣ ይሰበስባሉ፡፡
5. በ**ክፍለ *ሀገራት*** ውስጥ በውኃ ላይ ከሚደረግ ትራንስፖርት በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር ይጥላሉ፣ ይሰበስባሉ፡፡
6. በ**ክፍለ *ሀገራት*** ውስጥ በግል ባለቤትነት ሥር ካሉ ቤቶችና ሌሎች ንብረቶች በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር ይጥላሉ፣ ይሰበስባሉ፣ በባለቤትነታቸው ሥር ባሉ ቤቶችና ሌሎች ንብረቶች ላይ ኪራይ ያስከፍላሉ፡፡
7. በ**ክፍለ *ሀገራት*** ባለቤትነት ሥር በሚገኙ የልማት ድርጅቶች ላይ የንግድ ትርፍ፣ የሥራ ግብር፣ የሽያጭና ኤክሳይስ ታክስ ይጥላሉ፣ ይሰበስባሉ፡፡
8. **ክፍለ *ሀገራት*** በማዕድን ሥራዎች ላይ የማዕድን ገቢ ግብር፣ ክፍያዎች ይጥላሉ፣ ይሰበስባሉ፡፡
9. በ**ክፍለ *ሀገራት*** አካላት ከሚሰጡ ፈቃዶችና አገልግሎቶች የሚመነጩ ክፍያዎች ይወስናሉ፣ ይሰበስባሉ፡፡
10. **ክፍለ *ሀገራት*** ከደን የሚገኝ ክፍያ ይወስናሉ፣ ይሰበስባሉ፡፡

## *አንቀጽ 78*

## *የጋራ የታክስና የግብር ሥልጣን*

1. የፌዴራል መንግሥትና **ክፍለ ሀገራት** በጋራ በሚያቋቁሟቸው የልማት ድርጅቶች ላይ የንግድ ትርፍ ግብር፣ የሥራ ግብር፣ የሽያጭና የኤክሳይስ ታክስ በጋራ ይጥላሉ፣ ይሰበስባሉ፡፡
2. በድርጅቶች የንግድ ትርፍ ላይ እና በባለ አክሲዮኖች የትርፍ ድርሻ ላይ ግብርና የሽያጭ ታክስ በጋራ ይጥላሉ፣ ይሰበስባሉ፡፡
3. በከፍተኛ የማዕድን ሥራዎችና በማናቸውም የፔትሮሊየምና የጋዝ ሥራዎች ላይ የገቢ ግብር ክፍያዎች በጋራ ይጥላሉ፣ ይሰበስባሉ፡፡

# አንቀጽ 79

# ተለይተው ስላልተሰጡ የታክስ እና የግብር ሥልጣኖች

በዚህ **በሕገ-ኢትዮጵያ** ተለይተው ያልተሰጡ ታክስና ግብር የመጣል ሥልጣኖችን በሚመለከት የፌዴሬሽኑ ምክር ቤትና የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በጋራ ስብሰባ በሁለት ሦስተኛ ድምጽ ይወስናሉ፡፡

# አንቀጽ 80

# የታክስና የግብር አጣጣል መርሆዎች

1. **ክፍለ ሀገራት**ና የፌዴራሉ መንግሥት ታክስና ግብር በሚጥሉበት ጊዜ የሚጠየቀው ታክስና ግብር ከምንጩ ጋር የተያያዘና በአግባቡ ተጠንቶ የተወሰነ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡
2. በመካከላቸው የሚኖረውን መልካም ግንኙነት የማይጐዳና ከሚቀርበው አገልግሎት ጋር ተመጣጣኝ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡
3. ለትርፍ የቆመ ድርጅት ካልሆነ በስተቀር **ክፍለ ሀገራት**ና በፌዴራሉ መንግሥት ንብረት ላይ፣ የፌዴራሉ መንግሥትም በ**ክፍለ ሀገራት** ንብረት ላይ ግብር ወይም ቀረጥ የማስከፈል ሥልጣን አይኖራቸውም፡፡

# አንቀጽ 81

# የኢትዮጵያ የኦዲት ጀኔራል

**የኢትዮጵያ የኦዲት ጀኔራል በቀጥታ በሕዝብ በ13ቱም ክፍለ ሀገር ተወዳድሮ ለ4 አመት አገልግሎትና ለሁለት አመት ተርም (የጊዜ ገደብ) ይመረጣል።**

## ዋናው ኦዲተር

1. የኢትዮጵያ **ኦዲተር ጀኔራል ለ4ዓመት** አገልግሎት በቀጥታ ከ13ቱ ክፍለ ሀገራት ተወዳድሮ በቀጥታ በሕዝብ ይመረጣል።
2. ዋናው ኦዲተር የፌዴራሉን የሚኒስቴርና ሌሎች መሥሪያ ቤቶች ሂሳቦች በመቆጣጠር በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተመደበው ዓመታዊ በጀት፣ በበጀት ዓመቱ ለተሰሩት ሥራዎች በሚገባ መዋሉን መርምሮ ለምክር ቤቱ ሪፖርት ያቀርባል፡፡
3. ዋናው ኦዲተር የመሥሪያ ቤቱን በጀት በቀጥታ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ ያስጸድቃል፡፡
4. የዋናው ኦዲተር ዝርዝር ተግባር በሕግ ይወሰናል፡፡

# አንቀጽ 82

## የምርጫ ቦርድ

1. በፌዴራልና በ**ክፍለ ሀገራት የምርጫ ቦርድ** ነጻና ትክክለኛ ምርጫ በገለልተኝነት እንዲያካሂድ ከማንኛውም ተጽእኖ ነጻ የሆነ **ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ** ይቋቋማል፡፡
2. **ምርጫ ማጭበርበር በሕገ-ኢትዮጵያ በ15 ዓመት ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ የፈደራል መንግስት ወንጀል ነው። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡**

# አንቀጽ 83

## የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን

1. የሀገሪቱን የሕዝብ ቁጥር በየጊዜው የሚያጠናና ቆጠራ የሚያካሂድ የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን ይኖራል፡፡
2. የኮሚሽኑ አባላት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሾማሉ፡፡
3. ኮሚሽኑ ዋና ጸሐፊ፣ አስፈላጊ ባለሙያዎችና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡
4. የኮሚሽኑ ዓመታዊ በጀት በቀጥታ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርቦ ይጸድቃል፡፡
5. የሕዝብ ቆጠራ በየአሥር ዓመቱ ይካሔዳል፡፡ በውጤቱም መሰረት የምርጫ ቦርድ በሚያቀርበው ረቂቅ መሠረት የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት ይወስናል፡፡
6. የኮሚሽኑ ተጠሪነት ለሕዝብ ተወካዮቸ ምክር ቤት ነው፡፡ ስለ ሥራው አፈጻጸም በየጊዜው ለምክር ቤቱ ሪፖርት ያቀርባል፡፡
7. ብሔራዊ የሕዝብ ቆጠራ የየክፍለ ሀገሩ ነዋሪዎች ሕዝብ ቁጥር መሠረት ያደረገ ብቻ ነው።
8. በብሔራዊ የሕዝብ ቆጠራ ውስጥ የየክፍለ ሀገሩ ነዋሪዎች ሕዝብ መካከል **የዘር፣**

   **የጎሳ ስም** ፣ እና **የቀለም ልዩነት ለይቶ መቁጠር በሕገ-ኢትዮጵያ ፈጽሞ የተከለከለ** ነው።

# አንቀጽ 84

# <u>የሕገ- ኢትዮጵያ ማሻሻያ ሐሳብን ስለማመንጨት</u>

**የሕገ- ኢትዮድያ** ማሻሻያ ሐሳብ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሁለት ሦስተኛ ድምጽ የደገፈው፣ የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት በሁለት ሦስተኛ ድምጽ የደገፈው ወይም ከፌዴሬሽኑ አባል **ክፍለ ሀገራት** ውስጥ አንድ ሦስተኛው የ**ክፍለ ሀገራት** ምክር ቤቶች በድምጽ ብልጫ የደገፉት ከሆነ ለውይይትና ለውሳኔ ለመላው ሕዝብና መሻሻል ለሚመለከታቸው የ**ክፍለ ሀገራት** ይቀርባል፡፡

# አንቀጽ 85

# <u>ሕገ-ኢትዮጵያን</u> ስለማሻሻል

ሀ) ሁሉም **ክፍለ ሀገራት** ምክር ቤቶች የቀረበውን ማሻሻያ በድምጽ ብልጫ ሲያጸድቁት፣

ለ) የፌዴራሉ መንግሥት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሁለት ሦስተኛ ድምጽ የቀረበውን ማሻሻያ ሲያጸድቀው፣ እና

ሐ) የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት በሁለት ሦስተኛ ድምጽ ማሻሻያውን ሲያጸድቀው ነው፡፡

መ) የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት በጋራ ስብሰባ በሁለት ሦስተኛ ድምጽ የቀረበውን ማሻሻያ ሲያጸድቁት፣ እና

ሠ) ከፌዴሬሽኑ አባል **ክፍለ *ሀገራት*** ምክር ቤቶች ውስጥ የሁለት ሦስተኛ **ክፍለ *ሀገራት*** ምክር ቤቶች በድምጽ ብልጫ የቀረበውን ማሻሻያ ሲያጸድቁት ነው፡፡

# አንቀጽ 86

# በሕገ- ኢትዮጵያ መሠረት የመገንጠል

# ጥያቄ ማንሳት ወንጀል ነው

1) በፌዴራል ዲሞክራቲክ ሪፑብልክ ኢትዮድያ ሕገ-ኢትዮጵያ መሠረት 13ቱ ክፍለ ሀገራት በዕኩልነት የጋራ ሀብት ድርሻቸውን የሚጋሩ ሲሆን በጠላት ተንኮል ተነሳስተው ለመገንጠል ጥያቄ የሚያስነሱ ድርጅቶች ቢፈጠሩ ሕገ-ኢትዮድያን በመጻረር ወንጀል በፌዴራል መንግስት ከፍተኛ ቅጣት መቀበል አለባቸው።

# አንቀጽ 87

# ስለ ከነማ ምርጫ (ከተማ ነዋሪዎች ማህበር)

1) በሕገ- ኢትዮድያ መሠረት በፌዴራል ዲሞክራቲክ ሪፑብሊክ ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት

ትላልቅና ትናንሽ ከተሞች በክፍለ ሀገር፥ በአውራጃ፥ በወረዳ፥ በቀበሌ፥ እና በገበሬ ማህበራት ያለ ሕዝብ መሪውን ለ4 ዓመት በቀጥታ ሕዝቡ ይመርጣል።

# አንቀጽ 88

# ፌደራል ዲሞክራቲክ ሪፑብሊክ ኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት ብሔራዊ ፍርድ ቤት

ሀ/ የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት ብሔራዊ ፍርድ ቤት ዓለም ዓቀፋዊ ደረጃ በጠበቀ መልኩ በአገራችን ላይ ለሚነሱ ችግሮች፣ በፍርድ ቤቶች መካከል ግጭቶች ቢነሱ፣ በአስተዳደርና በፍርድ ቤት መካከል ግጭት ቢነሳ፣ በፌደራልና በክፍለ ሀገር መካከል ችግር ቢነሳ፣ መንስኤውን በማጣራ፣ አስፈላጊውን ውሳኔ በመስጠት ለጉዳዩ መፍትሄ የሚያስገኝ ሙሉ ሥልጣን ያለው ከፍተኛ ብሔራዊ ፍርድ ቤት ነው።

ለ/ የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት ብሔራዊ ፍርድ ቤት በአገራችን ላይ በትልቁም ሆነ በትንሹ ከተቋቋሙት የብሔራዊ ምርጫ ጣቢያዎች ላይ የሚከሰቱትን የምርጫ መዛባት በማጣራት ለምርጫ መዛባት ተጠያቂ ለሆኑ ግለሰቦች ፕሬዚዴንትን ጨምሮ ጥፋታቸው በመረጃ ከተረጋገጠ በሕገ-ኢትዮጵያ ላይ በተደነገገው ምርጫ ማጭበርበር ወንጀል መሠረት የፍርድ ውሳኔ ለመስጠት ሙሉ ሥልጣን ያለው ገለልተኛ የሕግ የበላይነትን የሚያስከብር የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት ከፍተኛ ብሔራዊ ፍርድ ቤት ነው።

ሐ/ የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት ከፍተኛ ብሔራዊ ፍርድ ቤት በዋናነት በሚከተሉት የሕግ የበላይነት ጥሰት ላይ በማተኮር ለሚነሱ ችግሮችን መርምሮ አስፈላጊውን ውሳኔ ለመስጠት ሙሉ ሥልጣን ያለው ብሔራዊ ፍርድ ቤት ነው። የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት ከፍተኛ ብሔራዊ ፍርድ ቤት አራት ዓበይት ተግባራት ይኖሩታል።

1) በፍርድ ቤቶችና በቢሮኪራሲ ላይ የሚነሱ ችግሮች ማቃለል፣
2) በፌደራል ፍርድ ቤትና በክፍለ ሀገር ፍርድ ቤት መካከል የሚነሱ ችግሮችን ማቃለል፣
3) በመደበኛ ፍርድ ቤትና በሕግ የበላይነት ፍርድ ቤት መካከል የሚነሱ ችግሮችን ማቃለል፣

4) በክፍለ ሀገር አስተዳደርና በፌደራል መንግሥት መካከል የሚከሰቱ ችግሮችን የማቃለል ሙሉ ሥልጣን ያለው የኢትዮድያ የሕግ የበላይነት ከፍተኛ ብሔራዊ ፍርድ ቤት ነው።

የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት ብሔራዊ ፍርድ ቤት፣ በአንድ ሊቀመንበር የሚመራ አዲስ አበባን ጨምሮ ከ13 ክፍለ ሀገር በሕዝብ ለሕዝብ የተመረጡ 14 የሕዝብ ዳኞችን ያቀፈ ገለልተኛ ብሔራዊ ፍርድ ቤት ነው።

የኢትዮድጵያ የሕግ የበላይነት ብሔራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች፣ የአገልግሎት ዘመናቸው ለስምንት ዓመት ሲሆን እንደገና ለመመረጥ በየስምንት ዓመት መፎካከር ይችላሉ። መመዘኛውም ፤

1) ዕድሜ ከ35 ዓመት በላይ፣
2) በሕዝብ አስተዳደር መልካም ሰነ ምግባርና በሥራው መልካም ውጤት ያስገኘ መሆኑ የተመሰከረለት ፤
3) ከመንግሥትና ከፖለቲካ ድርጅቶች አካል ነጻ የሆነ፣
4) ተፎካካሪዎች ሁሉ ሊቀመንበሩን ጨምሮ የሕግ ሙያ ያላቸውና ቢያንስ ለአምስት ዓመት በሙያቸው የሠሩ መሆን አለባቸው።

# አንቀጽ 89
# የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት ኮሚሽን

1) የኢትዮድያ የሕግ የበላይነት ኮሚሽን በሕገ-ኢትዮድያ ውስጥ በምዕራፍ አንድ ላይ ከተደነገጉት ከሦስት ዋና የመንግሥት አካላት ፈጽሞ የተለየ በቀጥታ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ለሕዝብ የተመረጡ የሕዝብ ተወካዮችን የያዘ ከሦስቱም ዋና የመንግሥት አካል ጋር ዕኩል የሆነ ሙሉ ሥልጣን ያለው ነው።
2) የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት ኮሚሽን ለአገራችን አሁን ላለውና ለሚመጣው ትውልድ ነፃና ገለልተኛ የሆነ፣ ከማናቸውም ፖለቲካ ድርጅት ግንኙት የሌለው፣ የአገራችንን የሕግ የበላይነት ሥልጣን ሙሉ በሙሉ በሥራ ላይ ለማዋል፣ በአገራችን ውስጥ ከፍተኛ ሥልጣን ያለው ኮሚሽን ነው።
3) የኢትዮድያ የሕግ የበላይነት ኮሚሽን ማንኛውም የኢትዮድያ ተወላጅ የተወለደበትና የሚኖርበት ሥፍራ ሁሉ የባለቤትነት ሙሉ መብት እንዳለው ለማስጠበቅ፣ በማንኛውም የኢትዮድያ ተወላጅ ላይ የወገን፣ የጎሣ፣ የጾታ፣ የቀለም፣ እና የኃይማኖት ልዩነት ማድረግ በሕግ የሚያስቀጣ ዓለም አቀፋዊ ወንጀል መሆኑን የሚገልጽና የሚከታተል ከፍተኛ ሥልጣን ያለው ኮሚሽን ነው።

4) የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት ኮሚሽን በሕጋችን ውስጥ በአንቀጽ 89 ላይ የተደነገገው በዋናነት ሥርዓታችን ዓለም ዓቀፋዊ የዲሞክራሲ ሥርዓት መስፈርቶችን ያሟላ መሆኑን ለመግለጽ ነው።

የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት ኮሚሽን ከመንግሥትና ከፖለቲካ ድርጅቶች ነፃና ገለልተኛ የሆነ በራሱ ሙሉ ሥልጣን ያለው በሕዝብ ለሕዝብ የተመረጡ አራት ነፃና ገለልተኛ የሆኑ ኮሚሽኖችን ያቀፈ ሙሉ የመንግሥት አካል ነው።

እነሱም፣ 1) የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት የሕዝብ አገልግሎት ኮሚሽን፣
2) የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት የምርጫ ኮሚሽን፣
3) የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት የቁጥጥር ኮሚሽን፣
4) የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ናቸው።

የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት የሕዝብ አገልግሎት ኮሚሽን፣

1) ይህ ኮሚሽን ከማናቸውም ከመንግሥት አካልና ከፖለቲካ ድርጅቶች ገለልተኛ የሆነ በቀጥታ በሕዝብ ለሕዝብ የተመረጠ ከመንግሥት ዕኩል ሙሉ ሥልጣን ያለው ኮሚሽን ነው።

2) የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት የሕዝብ አገልግሎት ኮሚሽን፣ የአገራችንን የሕግ የበላይነትን በሚመለከት ማንኛውንም ሕዝባዊ አገልግሎት፣ የመንግሥት ዋና መሥሪያ ቤቶች፣ የመንግሥት ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች፣ የመንግሥት ወኪሎች እና ኮርፖሬሽኖች፣ የአገሪቱ ፕሬዚዴንትን ጨምሮ የሕግ የበላይነትን ተላልፈው ከተገኙ ተከታትሎ ክስ በመመሥረት ማስቀጣት የሚችል በአገራችን ውስጥ ትልቅ ሥልጣን ያለው ገለልተኛ የሆነ የሕግ የበላይነት ኮሚሽን ነው።

3) የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት የሕዝብ አገልግሎት ኮሚሽን፣ በማዕከላዊነት ሆኖ ማንኛውንም ሕገወጥ ተግባራትን እየተቆጣጠረ፣ በተጨማሪም ለሕዝባችን ስለ ዲሞክራሲ ዕውቀት እያስተማረ መሠረታዊ መብታችንን ከመንግሥትና ከመንግሥት ወኪሎች ሁሉ ማግኘት የሚገባንን ነገሮች በሙሉ በሕጋዊ መንገድ እንዲሟላ የደርጋል። በመቀጠልም በሕገ- ኢትዮጵያ ውስጥ የተደነገጉትን የሰብዓዊ መብቶችና ጥቅሞች በሙሉ በሕጋዊ መንገድ እንዲሟሉ ያደርጋል።

4) የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት የሕዝብ አገልግሎት ኮሚሽን፣ ማንኛውም የሕግ የበላይነት ጥሰቶች እንዳይታዩ ግልጽ የሆነ ተጠያቂነትና ኃላፊነት እንዲኖራቸው የማድረግ ሙሉ ሥልጣን ያለው ገለልተኛ ኮሚሽን ነው።

5) የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት የሕዝብ አገልግሎት ኮሚሽን፣ በአገራችን ውስጥ ሁሉም የአገራችን ዜጋ በማንኛውም የአገራችን ክፍል የመኖርና ዕኩል የሥራ ዕድል እንዲኖረውና ምንም ዓይነት ልዩነት እንዳይደረግበት ወኪሎችም ሆኑ፣ ዋና የመንግሥት መሥሪያ

ቤቶችን ጨምሮ በሕግ ጥሰት የሚደርስን አድልዎ ለመቆጣጠር ሙሉ ሥልጣን ያለው ገለልተኛ ኮሚሽን ነው።

6) የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት የሕዝብ አገልግሎት ኮሚሽን፣ በአንድ ሊቀመንበር የሚመራ አዲስ አበባን ጨምሮ ከ13 ክፍለ ሀገር በሕዝብ ለሕዝብ የተመረጡ 14 የሕዝብ ወኪሎችን ያቀፈ ገለልተኛ የሆነ ኮሚሽን ነው።

7) የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት የሕዝብ አገልግሎት ኮሚሽን፣ የአገልግሎት ዘመናቸው ለስምንት ዓመት ሲሆን እንደገና ለመመረጥ በየስምንት ዓመት መፎካከር ይችላሉ።

መመዘኛውም ፤

5) ዕድሜ ከ35 ዓመት በላይ፣
6) በሕዝብ አስተዳደር መልካም ሥነ ምግባርና በሥራው መልካም ውጤት ያስገኘ መሆኑ የተመሰከረለት ፤
7) ከመንግሥትና ከፖለቲካ ድርጅቶች አካል ነጻ የሆነ፣
8) ተፎካካሪዎች ሁሉ ሊቀ መንበሩን ጨምሮ የሕግ ሙያ ያላቸውና ቢያንስ ለአምስት ዓመት በሙያቸው የሠሩ መሆን አለባቸው።

የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት የምርጫ ኮሚሽን፣

የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት የምርጫ ኮሚሽን፣ ከመንግሥትና ከፖለቲካ ድርጅቶች ገለልተኛና ነፃ የሆነ፣ ማንኛውንም የሕግ የበላይነትን የሚመለከት ነገር ሁሉ የመቆጠጣር ሙሉ ሥልጣን ያለው ኮሚሽን ነው።

እነዚህም፣ የምርጫ መዛባት እንዳይኖረው የሚቆጣጠርና የምርጫ ጣቢያዎችን የሚያዘጋጅ ተመራጮችን የሚመዘግብ ከ3ቱ ማዕከላዊ መንግሥት ገለልተኛ የሆነ ሙሉ ሥልጣን ያለው ኮሚሽን ነው።

የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት የምርጫ ኮሚሽን ዋና የሥራ ድርሻ፣

1) የሕግ የበላይነት ረቂቆች በብሔራዊ ሬፈረንደም ብቻ እንዲፀድቁ ያደርጋል።
2) የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት ምርጫ ጊዜ በቂ ፖሊሲና በቂ ምስክሮችን በመመደብ የመቆጣጠር ሙሉ ሥልጣን ያለው ከመንግሥት ገለልተኛ የሆነ ኮሚሽን ነው።
3) ለምርጫ የተመዘገቡትን የፖለቲካ ድርጅቶችን ሕጋዊነታቸውን ያጣራል።
4) ብሔራዊ የፕሬዚዴንት ምርጫ ጊዜ ማጭበርበር እንዳይኖር ከዓለም ዓቀፋዊ ሕብረተሰብ ታዛቢዎችን ጨምሮ ጥብቅ የሆነ ቁጥጥር እንዲደረግ የማስፈጸም ሙሉ ሥልጣን ያለው ኮሚሽን ነው።

5) ምርጫ የማጭበርበር ጥፋት የተገኘበት አካል የአገሪቱን ፕሬዚዴንት ጨምሮ፣ በሕገ-ኢትዮጵያ በአንቀጽ 82 ላይ በተደነገገው መሠረት ለፍርድ እንዲቀርብ ወደ ኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት ፍርድ ቤት በአስቸኳይ ያቀርባል።
6) የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት የምርጫ ኮሚሽን፣ በአንድ ሊቀመንበር የሚመራ አዲስ አበባን ጨምሮ ከ13 ክፍለ ሀገር በሕዝብ ለሕዝብ የተመረጡ 14 የሕዝብ ወኪሎችን ያቀፈ ገለልተኛ የሆነ ኮሚሽን ነው።
7) የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት የምርጫ ኮሚሽን፣ የአገልግሎት ዘመናቸው ለስምንት ዓመት ሲሆን እንደገና ለመመረጥ በየስምንት ዓመት መፎካከር ይችላሉ።

መመዘኛውም ፤

8) ዕድሜ ከ35 ዓመት በላይ፣
9) በሕዝብ አስተዳደር መልካም ሥነ ምግባርና በሥራው መልካም ውጤት ያስገኘ መሆኑ የተመሰከረለት ፤
10) ከመንግሥትና ከፖለቲካ ድርጅቶች አካል ነጻ የሆነ፣
11) ተፎካካሪዎች ሁሉ ሊቀመንበሩን ጨምሮ የሕግ ሙያ ያላቸውና ቢያንስ ለአምስት ዓመት በሙያቸው የሠሩ መሆን አለባቸው።

የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት የቁጥጥር ኮሚሽን፣

ይህ ኮሚሽን የፖለቲካ ቀውስ በአገሪቷ ላይ ሲከሰት በቂ ቁጥጥር በማድረግ፣ ማንኛውንም አካል የሕግ የበላይነት ምርጫ ወጭና ገቢ ሂሳብ መርምሮ የመንግሥት ወኪሎችን ሁሉ የአገሪቱን ፕሬዚዴንት ጨምሮ ተጠያቂ የሆነውን ክፍል ወደ ኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት ፍርድ ቤት ማቅረብ የሚችል ሙሉ ሥልጣን ያለው ገለልተኛ የሆነ ኮሚሽን ነው።

የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት የቁጥጥር ኮሚሽን በዋናነት የሚያከናወናቸው፣

1) የመንግሥትና የሕዝብ ገንዘብ በሕገወጥ መንገድ የሚደረግ ምዝበራ ቁጥጥር ለማድረግ ሙሉ ሥልጣን ያለው ኮሚሽን ነው።
2) ዓመታዊ የአገሪቷን ሂሳብ ሪፖርት ለሕዝብ ምክርቤት፣ ለኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት ብሔራዊ ፍርድ ቤትና ለፕሬዚዴንት ያቀርባል።
3) የመንግሥት አሠራር ጥንካሬና ድካም ሪፖርት ያደርጋል፣ በሚድያም ለአገሪቱ ሕዝብ ግልጽ ያደርጋል።
4) በአጠቃላይ ለኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት ሥራ የተከናወኑትን የሂሳብ ሰነዶች አጠናቅሮ ሪፖርት ያቀርባል።
5) ማንኛውንም የተዛባ የአሠራር ወንጀል በ60 ቀን ውስጥ አጠናቅሮ ለኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት ብሔራዊ ፍርድ ቤትና ለመደበኛ ፍርድ ቤት ያቀርባል።

6) የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት የቁጥጥር ኮሚሽን በአንድ ሊቀመንበር የሚመራ አዲስ አበባን ጨምሮ ከ13 ክፍለ ሀገር በሕዝብ ለሕዝብ የተመረጡ 14 የሕዝብ ወኪሎችን ያቀፈ ገለልተኛ የሆነ ኮሚሽን ነው።
7) የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት የቁጥጥር ኮሚሽን የአገልግሎት ዘመናቸው ለስምንት ዓመት ሲሆን እንደገና ለመመረጥ በየስምንት ዓመት መፎካከር ይችላሉ።

መመዘኛውም ፣

8) ዕድሜ ከ35 ዓመት በላይ፣
9) በሕዝብ አስተዳደር መልካም ሥነ ምግባርና በሥራው መልካም ውጤት ያስገኘ መሆኑ የተመሰከረለት ፣
10) ከመንግሥትና ከፖለቲካ ድርጅቶች አካል ነጻ የሆነ ፣
11) ተፎካካሪዎች ሁሉ ሊቀመንበሩን ጨምሮ የሕግ ሙያ ያላቸውና ቢያንስ ለአምስት ዓመት በሙያቸው የሠሩ መሆን አለባቸው።

የኢትዮድያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን፣

1) የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን፣ ከመንግሥትና ከፖለትካ ድርጅቶች ነጻና ገለልተኛ የሆነ ኮሚሽን ነው።
2) የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ዋና ሥልጣን በአገራችን ውስጥ ዓለም ዓቀፋዊ ሰብዓዊ የመብት ጥሰትን ከዓለም መንግሥታትና ከአገራችን የሕግ የበላይነት ብሔራዊ ፍርድ ቤት ጋር በመተባበር ሰብዓዊ የመብት ወንጀሎችን በመከታተል ሪፖርት ያቀርባል።
3) በአገር ውስጥና በውጭ አገር ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ሰብዓዊ መብታቸው የተጠበቀ እንዲሆን ከዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ጋር አገራችንን ወክሎ የሚሠራ ነፃና ገለልተኛ ኮሚሽን ነው።
4) ለሰብዓዊ መብት ጥሰት ሁሉም ኢትዮድያዊ ሕጋዊ ፍርድ እንዲያገኙ ይሠራል።
5) እስር ቤቶች ለሰው ልጅ አመቺ ሳይሆን የቅጣት ሥፍራ እንዲሆን ተደርገው የተሰሩትን ይቆጣጠራል።
6) የሰብዓዊ መብት ጥሰት ጉዳይ መረጃው ትክክለኛ መሆኑን ያጣራል።
7) ሰብዓዊ መብት ጥሰት የደረሰባቸው ግለሰቦችን ጉዳይ በአስቸኳይ ለፍርድ እንዲቀርቡና ተገቢውን ካሣ ለግለሰቡና ለቤተሰቦቻቸው ጭምር እንዲከፈላቸው ያደርጋል።
8) ከዓለም ዓቀፍ ሰብዓዊ መብት ተከራካሪ ኮሚሽን ጋር የተሳሰረ ግንኙነት በመፍጠር የኢትዮጵያ መንግሥት በሕዝባችን ላይ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ወንጀል ከፈጸመ በዓለም ዓቀፋዊ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ጋር በመተባበር ሕጋዊ ፍርድ እንዲያገኝ ያደርጋል።

9) ያለ በቂ መረጃ ማንም የኢትዮጵያ ዜጋ እንዳይከሰስ በአገራችን ውስጥና በውጭ አገር ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ሙሉ ዋስትና እንዲኖራቸው ያደርጋል።
10) የኢትዮጵያ ሰብዓዊ ሙብት ኮሚሽን በአንድ ሊቀ መንበር የሚመራ አዲስ አበባን ጨምሮ ከ13 ክፍለ ሀገር በሕዝብ ለሕዝብ የተመረጡ 14 የሕዝብ ወኪሎችን ያቀፈ ገለልተኛ የሆነ ኮሚሽን ነው።
11) የኢትዮጵያ ሰብአዊ ሙብት ኮሚሽን የአገልግሎት ዘመናቸው ለስምንት ዓመት ሲሆን እንደገና ለመመረጥ በየስምንት ዓመት መፎካከር ይችላሉ።
12) መመዘኛውም ፣
13) ዕድሜ ከ35 ዓመት በላይ፣
14) በሕዝብ አስተዳደር መልካም ሰነ ምግባርና በሥራው መልካም ውጤት ያስገኘ መሆኑ የተመሰከረለት ፣
15) ከመንግሥትና ከፖለቲካ ድርጅቶች አካል ነጻ የሆነ ፣
16) ተፎካካሪዎች ሁሉ ሊቀመንበሩን ጨምሮ የሕግ ሙያ ያላቸውና ቢያንስ ለአምስት ዓመት በሙያቸው የሠሩ መሆን አለባቸው።

# አንቀጽ 90
# የመጨረሻ ሕጋዊ ዕውቅና ስላለው ቅጇ

1) ሕገ ኢትዮጵያ በሁለቱም በአማርኛና በእንግሊዘኛ የተደነገጉት ሕጎች በኢትዮጵያ ሕዝብ ድምፅ ብልጫ በሪፈረንደም ከጸደቀበት ስዓት ጀምሮ በአገራችን ላይ የመጨረሻ ከፍተኛ ሥልጣን ያለው ሰነድ ይሆናል።
2) ሕገ ኢትዮጵያ በሁለቱም በአማርኛና በእንግሊዘኛ የተደነገጉት ሕጎች በኢትዮጵያ ሕዝብ ድምፅ ብልጫ በሪፈረንደም ከጸደቀበት ስዓት ጀምሮ በአገራችን ላይ ፕሬዚዴንቱን ጨምሮ ሁሉም ሰው ከሕግ የበታች ነው።
3) ሕገ ኢትዮጵያ በሁለቱም በአማርኛና በእንግሊዘኛ የተደነገጉት ሕጎች በኢትዮጵያ ሕዝብ ድምፅ ብልጫ በሪፈረንደም ከጸደቀበት ስዓት ጀምሮ በምድራችን ላይ ከሕጎች ሁሉ የበላይ ሕግ ነው
4) የሚቀጥለው ትውልድ ሕገ ኢትዮጵያን በሕዝብ ድምፅ ብልጫ ያሻሽል እንጂ በፍጹም መሻር የለበትም።

## የእግዜአብሔርን ቃል እናስታውስ!!

የእሥራኤል ልጆች ሆይ! እናንተ ለእኔ እንደ ኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁምን? ይላል እግዚአብሔር። አሞፅ (፱ ፥፯)

# በቅዱስ ቁርዓን ነብዩ መሃመድ

ኢትዮጵያን አትንኳት ይላል።